# አዲስ ዘመን

እናድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 071 ኅዳር 11 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ለመጀመሪያ ጊዜ ሶስት የታሸገ ውሃ አምራቾች

## ምርታቸውን ወደ ውጭ ሊልኩ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ካሉ የታሸገ ውሃ አምራች ፋብሪካዎች መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ ሶስት የታሸገ ውሃ አምራቾች ምርታቸውን ወደ ውጭ ሊልኩ ዝግጅት ማድረጋቸውን የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ። በአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የተገነባውና የታሸገ ውሃ ወደ ውጭ ለመላክ ዝግጅት እያደረገ የሚገኘው ስፖርት ውሃ ፋብሪካ ተመርቋል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል ፋብሪካውን ትናንት መርቀው ሲከፍቱ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ አካባቢዎች 110 የታሸገ ውሃ አምራች ፋብሪካዎች ፈቃድ አውጥተው እየሰሩ ይገኛል።

አጠቃላይ በአገሪቷ ካሉት የታሸገ ውሃ አምራች ፋብሪካዎች መካከል ወደ ምርት ከገባው ስፖርት ውሃ በተጨማሪ ሌሎች ሁለት ፋብሪካዎች የታሸገ ውሃ ለውጭ ገበያ ለማቅረብና የውጭ ምንዛሬ ለማምጣት የሚያስችል ዝግጅት አድርገዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት የውሃ ፋብሪካዎች በዓመት ዘጠኝ ነጥብ 75 ቢሊዮን ሊትር የታሸገ ውሃ እየተመረተ ይገኛል። ምርቱ ግን ካለው የሕዝብ ብዛት አንፃር አነስተኛ የሚባል ደረጃ ላይ ነው ብለዋል።

አገራችን ከራሷ አልፋ ለውጭ ገበያ በተለይም ለአረቡ ዓለምና ለጎረቤት አገራት የሚተርፍ የውሃ ሀብት አላት ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም የሚረዱ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉና ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭው ዓለም እንዲያቀርቡ አስፈላጊው ጥረት ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ መላኩ ገለጻ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሃ ለማምረት ብሎም ለውጭ አገራት ለመሸጥ ለሚፈልጉ ኢንቨስተሮች የተለያዩ ድጋፎችን እያደረገ ይገኛል። የታሸገ ውሃ ወደ ውጭ ለመላክ ዝግጅት ካደረጉ መካከል አንዱ የሆነው በበላያ ኢንዱስትሪ ሱልልታ ከተማ በአንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ብር የተገነባው ስፖርት ውሃ ትናንት ተመርቋል።

ለመጀመሪያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# ኢትዮጵያ ተለዋዋጭ የዓለም ሁኔታን የሚመጥን የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ይኖርባታል



**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡ - ኢትዮጵያ ተለዋዋጭ የዓለም ሁኔታ የሚመጥን የዲፕሎማሲ ሥርዓት ለመዘርጋት እየተጋች ቢሆንም አሁንም ጠንካራ ስራ መስራት ይኖርበታል ሲሉ የቀድሞ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ አስታወቁ፡፡

አቶ ኃይለማርያም የውጭ ግንኙነትና ብሔራዊ ጥቅም ዙሪያ ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መካከለኛና ከፍተኛ ዲፕሎማቶች በሱልልታ ከተማ በአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ እየተሰጠ ባለው ሥልጠና ላይ ትናንት ተገኝተው በሰጡት ማብራሪያ ፤ ኢትዮጵያ የቆየ የዲፕሎማሲ እውቀትና ልምድ አላት፡፡ ከዓለም ተለዋዋጭ ሁኔታ ጋር የራስ ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ከነበሩ ልምዶች ጠንካራዎቹን በማጎልበት አዳዲስ እሳቤዎችን እየጨመሩ መሄድ ወቅቱ የሚጠይቀው የዲፕሎማሲ አሰራር ነው ብለዋል፡፡

አገሪቱ በውጭ ግንኙነት ፖሊሲዋ ለብሔራዊ ጥቅሟ ሲባል አቋሟን የማትቀይርባቸው አንኳር ጉዳዮች አሏት ያሉት አቶ ኃይለማርያም፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከዓለም ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር ሊስተካከሉ የሚገቡ ጉዳዮች ስላሉ ተለዋዋጭ የዓለም ሁኔታን የሚመጥን የዲፕሎማሲ ስራ መስራት ይኖርብናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የዲፕሎማሲ ዋና ዓላማ በሰጥቶ መቀበል መርህ የሌላውን ጥቅም በማይጎዳ መልኩ የራስ ጥቅም ማስከበር መሆኑን የጠቀሱት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሃይለማሪያም፤ ያም ሆኖ በሃያላን አገር የሚዘወር ዓለም ውስጥ የራስ ጥቅም ማስከበር ውስብስብና ፈታኝ

ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



“የመንግሥት ተቋማትን ወደ ግል ማዞሩ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው”

\- የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ

ገጽ 4







ኢትዮጵያን ወደ አጎዋ ተጠቃሚነት እንድትመለስ ተጠየቀ

ገጽ 2

ዜና



# 170 ሺ ሰዎችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የውሃ ፕሮጀክቶች ስራ ጀመሩ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ደብረ ብርሃን፡- በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር 170 ሺ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ የሚያደረጉ የንፁህ መጠጥ ውሃና የንጽህና አገልግሎት መስጫ ፕሮጀክቶች ስራ መጀመራቸውን ፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ አስታወቀ።

በፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ የወሽ ፕሮግራም ማናጀር አቶ ወንደሰን አድማሱ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፕሮጀክቶቹ የተከናወኑት በሰሜን ሸዋና በኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር አጣዬና ሸዋሮቢት ከተማ በሚገኙ ስምንት ወረዳዎች ውስጥ ነው።

ከአጣዬና ሸዋሮቢት በተጨማሪ በደብረብረሃን ከተማ በግጭት ምክንያት ተፈናቅለው ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችም የንፁህ መጠጥ ውሃና የንፅህና አገልግሎት መስጫ ተቋማትም መገንባታቸውን ማናጀሩ ጠቁመዋል። በዚህም 170 ሺ የሚሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በእነዚህ ፕሮጀክቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አስታውቀዋል።

ፕሮጀክቶቹን አጠናቆ ለማስረከብ ስድስት ወር እንደፈጀ የተናገሩት ማናጀሩ፤ ለግንባታቸውም 70 ሚሊዮን ብር ወጪ መሆኑንና የፕሮጀክቱ ግንባታ ከዩኒሴፍ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እንደተከናወነም ገልጸዋል።

ከፕሮጀክቶቹ ውስጥ አስራ ስድስት የንጹህ መጠጥ ውሃ ግንባታዎችን በማህበረሰቡ ውስጥ የማስፋፋት ስራዎችና የመፀዳጃ ቤቶችን በተፈናቃይ መጠለያ ጣቢያዎችና በማህበረሰቡ ውስጥ የመገንባት ስራ እንደሚገኙበትም ማናጀሩ ጠቁመዋል።

በተጨማሪም አስር የሻወር ቤቶች በደብረብረሀን ከተማ ለሚገኙ ተፈናቃዮቹ መገንባታቸውን ማናጀሩ ተናግረዋል ። ህብረተሰቡ በቀጣይ የውሃ ተቋማትን በዘላቂነት እንዲጠቀም የአቅም ግንባታ ሥልጠና መሰጠቱንም አመልክተዋል።

በስምንቱ ወረዳዎች ውስጥ የውሃ ተቋማት ውስጥ ላሉ ባለሙያዎች የውሃ ጥራትን እንዲያረጋግጡ የሚያስችል ሥልጠና መሰጠቱን የገለጹት ማናጀሩ፤ በቀጣይም ፕሮጀክቶቹን ለማስፋፋት በፕላን ኢንተርናሽናል ኢትዮጵያ በኩል ተጨማሪ 35 ሚሊዮን ብር መመደቡን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቶቹ ተጠናቀው ወደ ስራ መግባታቸው በተለይ በአካባቢዎቹ ያለውን የንጹህ መጠጥ ውሃና የንጽህና ችግሮች እንደሚፈታም ነው የገለጹት።



# የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ትልልቅ ኢኮኖሚያዊ እድሎችን ለኢትዮጵያ ያመጣል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ትልልቅ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን ለኢትዮጵያ እንደሚያመጣ የኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን ገለጸ።

በኢትዮጵያ ማሪታይም ባለሥልጣን የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽህፈት ቤት የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ኃላፊው አቶ ተስመገን ይሁኔ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በድሬዳዋ ከተማ ተግባራዊ ያደረገችው ነፃ የንግድ ቀጣና ትልልቅ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን የሚያመጣ ነው። ነፃ ንግድ ቀጣና መኖሩም የውጭ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፣ የውጭ ንግድን በማነቃቃት እና በሥራ ዕድል ፈጠራ ትልልቅ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያላቸው እድሎችን ይፈጥራል።

በርካታ የዓለም አገራት ነፃ የንግድ ቀጣና አቋቁመው ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ እንደ ሱዳን፣ ጅቡቲ፣ ኬንያ እና ሱማሌ ላንድ ያሉ ጎረቤት አገራት የኢትዮጵያን ገበያ ታሳቢ ያደረገ ነፃ ንግድ ቀጣና እንዳላቸው ተናግረዋል።

በነፃ ንግድ ቀጣናው የኢትዮጵያን ተጠቃሚነት የበለጠ ለማሳደግ ፖሊሲ ተዘጋጅቶ መጠናቀቁን ጠቁመው፤ ፖሊሲውም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ጸድቋል ብለዋል።

የነፃ ንግድ ቀጣና ፖሊሲውም የአሰራር ሥርዓቱን በተሻለ መልኩ በማሳደግ አገልግሎቱን የተሳለጠ እንዲሆን ለማድረግ እገዛ እንደሚያደርግ ተናግረዋል።

ፖሊሲውም በዘርፉ ያሉ ችግሮችን በመለየት የሚፈቱበትን፣ ኃላፊነትን በሚገባ ለመወጣት እና የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ አሰራር በግልጽ እንዳስቀመጠ አንስተዋል።

ነፃ የንግድ ቀጣና ፖሊሲውን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል መመርያ እና የሕግ ማዕቀፍ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል። ነፃ የንግድ ቀጣና ሥርዓቱ ለኢትዮጵያ አዲስ በመሆኑ ወደ ነፃ የንግድ ቀጣናው ለሚገቡ ባለሀብቶች፣ ሰራተኞች እና የተቋሙ የሰው ኃይል ተከታታይ የሥልጠናና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት እንደሚገባም ገልጸዋል።

የሎጂስቲክስ ዘርፍ ባለሙያ የሆኑት አቶ እንዳልካቸው በቀለ፣ ከነፃ ንግድ ቀጣናው የሚገኘውን ተጠቃሚነት ለማሳደግ የቴሌኮም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል እና ሌሎች የመሰረተ ልማት አቅርቦት ላይ በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

የውጭ ባለሀብቶችን ወደ ነፃ ንግድ ቀጣናው ለመሳብም የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ወደ ስራ እንዲገቡ ማድረግም ሌላኛው ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን አንስተዋል።

እንደ ቱርክ፣ ቻይና፣ ታይዋን ያሉ በርካታ የዓለም አገራት ነፃ የንግድ ቀጣና ኢኮኖሚያዊ አቅጣጫን ተከትሎ ውጤታማ እንደሆኑ በመጥቀስ፤ የአገራቱን መልካም ተሞክሮ መውሰድ እንደሚጠቅምም መናገራቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

ኢትዮጵያ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነትን ከፈረሙ የአፍሪካ አገራት አንዷ መሆኗ ይታወሳል። ነፃ የንግድ ቀጣናን ማቋቋም የሚያስችል ጥናትና ልዩ ልዩ ዝግጅት ሲደረግ ከቆየ በኋላም በቅርቡም የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የድሬዳዋ ከተማ ነፃ የንግድ ቀጣናን በይፋ ስራ ማስጀመራቸው ይታወቃል።

# ኢትዮጵያ ወደ አጎዋ ተጠቃሚነት እንድትመለስ ተጠየቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


አዲስ አበባ፡- የአሜሪካ የኮንግረስ አባል ዶን ቤየር ኢትዮጵያ ወደ አፍሪካ ከቀረጥ ነጻ ንግድ ዕድል ድንጋጌ (አጎዋ) ተጠቃሚነት እንድትመለስ ለአገራቸው መንግሥት ጥያቄ አቀረቡ።

አጎዋ የኢትዮጵያና አሜሪካ የሁለትዮሽ ትብብርን ያጠናከረ ቁልፍ መሳሪያ ነውም ብለዋል። የኮንግረስ አባል ዶን ቤየር (ቨርጂኒያ ዴሞክራቲክ ፓርቲ) ለአሜሪካ የንግድ ተወካይ አምባሳደር ካትሪን ታይ ባጻፉት ደብዳቤ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሕወሓት ጋር የተፈራረመውን ስምምነት ተፈጻሚ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በስምምነቱ አማካኝነት መንግሥት ተኩስ በማቆምና ሰብአዊ እርዳታን ባልተገደበ መልኩ ተደራሽ እያደረገ መሆኑን አመልክተው፤ በዚሁ መሰረት የአሜሪካ መንግሥት ኢትዮጵያን ወደ የአፍሪካ የእድገትና ዕድል ድንጋጌ (አጎዋ) የመመለስን ጉዳት ሊያጤነው እንደሚገባ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የአጎዋ ተጠቃሚ በነበረችበት ወቅት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ከፍተኛ እድገት እንዲያሳይ፣ በ10 ሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች የስራ እድል የፈጠረና የሁለቱን አገራት የንግድ አጋርነት ለማሳደግ አስተዋጽኦ ማድረጉን አመልክተዋል።

ኢትዮጵያ ተጠቃሚነቷን ስታጣ በአጎዋ ጥላ ስር ምርታቸውን ወደ አሜሪካ ይልኩ የነበሩ ኩባንያዎች የማስፋፋፊያ እቅዳቸውን መተዋቸውንና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰራተኞችን መቀነሳቸውን ነው የኮንግረስ አባሉ ለአምባሳደር ካትሪን በጻፉት ደብዳቤ ገልጸው፤ኢትዮጵያን ከአጎዋ የማስወጣት ውሳኔ የሁለቱ አገራት ግንኙነት ላይ መቀዛቀዝ እንዲታይ ማድረጉንም ተናግረዋል።



ዶን ቤየር

አሜሪካ በኢትዮጵያ የአጎዋ ተጠቃሚነት በድጋሚ መመለስ ዙሪያ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር ውይይት እንዲያደርግ ዶን ቤየር ለአምባሳደር ካትሪን ጥሪ አቅርበዋል።

በአፍሪካ ሕብረት ጥላ ስር የተፈረመው የሰላም ስምምነት ተፈጻሚነት ኢትዮጵያን በፍጥነት ወደ አጎዋ ተጠቃሚነት ይመልሳታል ብለው እንደሚያምኑም ተናግረዋል።

የ72 ዓመቱ ዶን ቤየር የቨርጂኒያ ግዛትን ወክለው እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር ከ2015 ጀምሮ በኮንግረስ አባልነት እያገለገሉ ይገኛል።

በቅርቡ በተካሄደው የአሜሪካ የኢጋማሽ ዘመን ምርጫ(ሚድ ተርም ኢሌክሽን) በኮንግረስ አባልነት በድጋሚ ተመርጠዋል።

ዶን ቤየር 'የአሜሪካን ኢትዮጵያን ፐብሊክ አፌርስ ኮሚቴ' (ኤፓክ) የተሰኘው የፖለቲካ ተግባር ኮሚቴ በኢጋማሽ ዘመን ምርጫ ይሁንታ ከሰጣቸው 34 እጩዎች መካከል ይገኙበታል። በምርጫ ቅስቀሳቸው ወቅትም ኢትዮጵያን ወደ አጎዋ ተጠቃሚነት ለመመለስ አበክረው እንደሚሰሩ መግለጻቸው ይታወቃል።

የዴሞክራቲክ ፓርቲ አባል ዶን ቤየር የኢትዮጵያና አሜሪካ የሁለትዮሽ ትብብር እንዲጠናከር ገንቢ ሚና እየተጫወቱ እንደሚገኙም ይነገርላቸዋል። በሚኖሩበት ቨርጂኒያ ግዛት ከሚኖሩ በርካታ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር በየጊዜው ውይይት በማድረግ መልካም የሚባል ግንኙነት መገንባት ችለዋል ሲል የዘገበው ኢዜአ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሙስናን በመዋጋቱ ትግል ዜጎች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል!

በኢትዮጵያ ስር የሰደደ የኑሮ ውድነት እና ያልተገባ የዋጋ ንረት የዜጎች በተለይም በቋሚ ገቢና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ሰዎችን ህልውና መፈታተን ከጀመረ ውሎ አድሯል፡፡ ለዚህ የኑሮ ውድነት አንድ ምክንያት የሆነው ያልተገባ የዋጋ ንረት መፈጠር ምክንያት ተደርገው ከሚነሱ ጉዳዮች መካከል ደግሞ የኢኮኖሚ በተለይም በገበያው ላይ የሚሰራ አሻጥር በቀዳሚነት ይነሳል፡፡ ይሄን መሰል የገበያ አሻጥር የሚፈጠረው ደግሞ አንድም በዘርፉ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ባሉ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፤ ሁለተኛም በየቦታው ራሳቸውን የጎበዝ አለቃና ፈላጭ ቆራጭ አድርገው በሾሙ ደላሎች፤ ሦስተኛም በንግዱ ዘርፍ የተሰማሩ ገንዘብ አምላካቸው የሆኑ ግለሰቦች በሚፈጥሩት ያልተገባ የጥቅም ትስስር ምክንያት ነው፡፡

በመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ጥቂት የማይባሉ ሹመኞችና ባለሙያዎች ወር ቆጥረው የሚቀበሉት ደመወዝ ከሕዝብ የተሰበሰበ ሀብት መሆኑን ዘንግተው ባልተገባ ጥቅም ውስጥ ራሳቸውን ሲያስገቡና ሕዝብን እንዲያገለግሉ የተሰጣቸውን ታላቅ ኃላፊነት ቸል ሲሉ፤ ይልቁንም ለአገልግሎታቸው ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ከተገልጋይ ተጨማሪ የእጅ መንሻ ክፍያን ሲጠይቁ ይስተዋላል፡፡ ይሄ መጥፎ ልምምድ አድጎም ነው ዛሬ ላይ የገበያው ሰንሰለት በብልሹ አሰራር በአቋራጭና በአጭር ጊዜ ሀብት የመፍጠሪያ አውድ ሆኖ የሚታየው፡፡ ይሄን የማስተካከል ኃላፊነት የተጣለባቸው አንዳንድ በዘርፉ የመንግሥት መዋቅር ውስጥ ያሉ ግለሰቦችም ችግሩን ለመከላከል በኃላፊነት ከመስራት ይልቅ፤ ለችግሩ መባባስ ምክንያት በሚሆን መልኩ የጥቅም ተጋሪነታቸውን ሲያሳልጡ የሚታዩት እና ለተፈጠረው የገበያ ብልሽት እልባት መስጠት እንዳይቻል የሆነው፡፡

የግብይት አውዱ ዋና ተዋናይ የሆነው ቁጥሩ ቀላል የማይባል ከሰው ይልቅ ገንዘብ የሚገዛው ነጋዴም፤ ይሄንኑ የተቆጣጣሪውን አካል ለሕዝብ ሳይሆን ለጥቅም ማደር ከግምት በማስገባት “ተጠቅሜ ልጥቀምህ” በሚል የገንዘብ አምላኪነት እሳቤ ውስጥ ገብቶ ለመውጣት ተቸግሮ የሚታየው፡፡ እነዚህ የተቆጣጣሪ አካል እና ነጋዴው ናቸው ዛሬ ላይ በሕዝብ ላብና ደም ላይ የመቆመር ያልተገባ የጥቅም ትስስር ነው ዜጎች በኑሮ ውድነት እንዲፈተኑ፤ በየእለቱ መቆሚያ በሌለው መልኩ ከሚያሻቅበው የዋጋ ንረት ጋር ማደግ ያልቻሉ እልፍ ወገኖችን ሕልውና አደጋ ውስጥ እየከተቱ ያሉት፡፡

የእነዚህ ሁለት ተዋናዮች ጥምረት ደግሞ በራሱ በቀጥታ የሚከወን አይደለም፡፡ ይልቁንም ሁለቱም ከልባቸውም፣ ከሕሊናቸውም እንዳይሆኑ የሚያደርጉ አካሄዶችን በመከተል ገበያውንም፣ ግብይቱንም በመወሰን የሚያሳልጥላቸው አፋ ቅቤ የሚጠብስ ደላላ በመካከላቸው አለ፡፡ ይህ ደላላ ኪሱ የሚሞላው፣ ኑሮው የሚንደላቀቅ፣ የዘመኑ ችግርና ፈተና ፈጽሞ የሚደርስበት የማይመስለውን የፈረጠመ አቅም የፈጠረ ነው፡፡ የዜጎች ችግርና መከራ ሳይሆን የራሱ ጥቅም ቀጣይነት የሚያሳስበው፤ ከነጋዴው ከፍ ያለ የአቋራጭ ትርፋማነት የሚያገኘው ኮሚሽን እንቅልፍ የሚነሳው፤ የመንግሥት መዋቅሩን ተጠቅሞ የሚፈጽማቸው የግብይት ሂደት መዛነፎች በምን መልኩ እንደሚሳኩለት እያሰበ ለተግባራዊነታቸው ረፍት የማያውቅ ነው፡፡

በዚህ መልኩ ነጋዴውን ከተቆጣጣሪው አካል በማገናኘት በአቋራጭ የተትረፈረፈ ሀብት ለማጋበስ መደላድል የሚፈጥረው ይሄ ደላላ ታዲያ፤ ነጋዴው በትርፍ እሳቤ ብቻ እንዲታወር፤ ተቆጣጣሪው አካልም በሚያገኘው መደለያ ላይ ብቻ ትኩረቱን እንዲያደርግና የሕዝብ ጥያቄና ብሶት እንዳይታየው ከፍ ያለ ሚና የሚጫወት ነው፡፡ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከሰሞኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ስለ ዘመኑ ሙስና ባስረዱበት ወቅት “... እውነት ነው፣ ሌብነት በጣም አታካች ነገር ሆኗል፡፡ በተለይ የገጠመንን ሀገራዊ ፈተና የገጠመንን ሀገራዊ ችግር እንደ እድል የወሰዱ ሰዎች ቀይ መስመር ያልነውን ሌብነት ቀይ ምንጣፍ አድርገውታል፡፡ ቀይ ምንጣፍ አድርገው በነጻነት የሚንሸራሸሩበት ሰዎች እየተፈጠሩ ሄደዋል፤...” ሲሉ መናገራቸውም ይሄንኑ የሚያረጋግጥ ሃቅ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አያይዘው እንዳመለከቱት ደግሞ፤ ይሄን አይነት ያልተገባ ጥቅም የማግኘት አካሄድና ሙስና በረቀቀና በተጠና መልኩ የሚፈጸም ነው፡፡ በመሆኑም ችግሩን በጥንቃቄና በተጠና መልኩ መፍታት በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደ መንግሥት የፀረ ሙስና ብሔራዊ ኮሚቴ አዋቅሮ ወደስራ እንዲገባ አድርጓል፡፡ ይህ መልካም ተግባር ቢሆንም፤ የዚህ ኮሚቴ ስራም ሆነ የመንግሥት አካሄድ ውጤታማ የሚሆነው የሕብረተሰቡ ንቁ ተሳትፎና እገዛ ሲታከልበት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዛሬ ላይ ዜጎች በእጅጉ የሚፈተኑበት የመልካም አስተዳደር ብቻ ሳይሆን፤ ሕልውናቸውን እየተፈታተነ ያለው የኑሮ ውድነት ገንግኖ መውጣት አንዱና ትልቁ ምክንያት ይሄው ያልተገባ ተጠቃሚነትን የመሻት የሙስና ተግባር ውጤት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡ በመሆኑም ሙስናን መዋጋት የከበደውን ኑሮ ማቃለያና ፍትሃዊነትን የማስፈን አንዱ መሳሪያ መሆኑን በመረዳት፤ ዜጎች መንግሥት ያቀረበውን ጥሪ ተቀብለው የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል!

---


**አዲስ ዘመን**

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


---

**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡**

# መንገዶች ሁሉ ወደ ሰላም ይወስዳሉ

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

እነሆ ! የሰላም አየር ሊነፍስ፣ የጦርነቱ እሳት ሊጠፋ ጊዜው ደርሷል። ስደት መፈናቀል፣ ርሀብና ስቃይ ‹‹ነበር›› ተብለው ሊጻፉ መንገዱ ጀምሯል። ሞትና ውድመት ፣ ለቅሶና ዋይታ ዝምታ ሊውጣቸው ከጫፍ ደርሷል። አሁን እነዚህን ቅስፈቶች የማናይ፣ የማንሰማበት ቅያስ ላይ ቆመናል።

ይህ መንገድ አቅጣጫው ወደ አንድ መስመር ይወስዳል። ምሪቱን ይዞ ለተጓዘ፣ ምልክቱን አይቶ ለተራመደ ደግሞ መዳረሻው አንድ አንድ ነው። ቀስቱ ከሰላም መንደር ያገባል። ወገግታው ጨለማን ገፎ ከንጋት ያደርሳል። ይህን የብርሀን መስመር የተከተሉ ሁሉ እፎይታቸው የበዛ፣ ተስፋቸው ያበበ ነው። የዘወትር፣ ህልማቸው ከራሳቸው ያድር ዘንድ መተማመኛን ይዘዋል።

ሰላም እስትንፋስ ላለው ሁሉ ታላቅ ዋጋ ያለው ዋስትና መሆኑ አያጠያይቅም። በተለይ ህይወታቸው በጦርነት እሳት የተፈጀ፣ ኑሯቸው በዚህ መቅሰፍት የተነጠቀ ወገኖች የሰላምን ትርጉም አሳምረው ያውቁታል። አገራችን ላለፉት ሁለት ዓመታት በጦርነት እጅጉን ስትፈተን ቆይታለች። ይህ መቅሰፍት የመዘዘው ጫፍም በቃላት ሊገለፁ የማይችሉ ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳቶችን አሳርፎብናል ። አሁንም ድረስ ጠባሳው ባልሻረው መቅሰፍት ብዙሀን ህይወታቸውን ተነጥቀዋል። ቤት ንብረት ወድሟል፣ ስደትና መፈናቀል አይሏል።

ይህ እውነታ ለዓመታት ሰላማዊ ሆኖ የኖረውን ህዝብ በእጅጉ ፈትኖታል። ለልማትና ብልጽግና ስትንደረደር የኖረችውን አገር ህልም አጨናግፏል። የጦርነቱ እሳት የበርካቶችን ኑሮና ህይወት የኋሊት እንደማራመዱ ኪሳረው የበዛ፣ ችግሩ የሰፋ ሆኖ ቀጥሏል ።

ዓመታትን ያስቆጠረው የጦርነት እሳት ይበቃ ዘንድም እስከዛሬ የሰላማዊ አማራጮች ሲሞከሩ ቆይተዋል። አስካሁን በነበሩ መልካም አጋጣሚዎች በአገራችን ሰላም ይሰፍን ዘንድ ሲጥሩ የቆዩ አካላት አሁን ድካማቸው ፍሬ ይዞ ከመልካም ውጤት ደርሰዋል።

የሰላምን ዋጋና ቱርፋት የማይሹ አንዳንድ ልበ ክፉዎች ግን ጦርነቱን እንደምክንያት ተጠቅመው ህልማቸውን ሲፈቱ ዓላማቸውን ሲያሳኩ ቆይተዋል። ለእነዚህ አካላት ጠብና ሁከት ደስታቸው፣ ግጭትና ጦርነት ህይወታቸው ነው። ደም በፈሰሰ ቁጥር ገቢያቸው ያድጋል። አገር ሲወድም፣ ህዝብ ሲያልቅ፣ መፈናቀል ሲያይል ቋታቸው በሀሴት ይሞላል።

እነሱ ሰላም ይሉትን ቃል አይወዱትም ። መግባባት፣ መስማማት ይሏቸው እውነቶች የመንገዳቸው ዕንቅፋት ናቸው። ሁሌም እግርን ከእግር እያጋጩ ጠልፎ በመጣል አባዜ ሲስቁ ይውላሉ። አንደበታቸውን ሞርደው የኪሳቸውን ጻጋ ሲያደልቡ ይሉኝታና ሀፍረትን አያውቁም።

በውጭ አገራት የሚኖሩ አንዳንድ ዳያስፖራ ተብዬዎች ንጹሀንን ከእሳት ማግደው በፍሙ ራሳቸውን ሲያሞቁ መዋላቸውን እንደጀብዱ ሲቆጥሩት ኖረዋል። ዛሬም ድረስ ለሰላም ያላቸው ንቀት ከአደባባይ አውሎ የውስጣቸውን ጉድ እያጋለጠው ይገኛል። ሰላምን አንፈልግም ባዮቹ ሁከት ናፋቂዎች አሁን በሰላም ስምምነቱ በእጅጉ ተከፍተዋል።

ሰላምን እንደጦር የሚፈሩት ሁከት ናፋቂዎች በግላቸው በከፈቷቸው የሚዲያ መረቦች ራሳቸውን ለመሸጥ ጦርነቱን ሲጠቀሙበት ኖረዋል። በየጊዜው በሚነዟቸው የሀሰት ትርክቶችም የበርካቶችን ልብ አሸፍተው ተከታዮችን ለማብዛት ሲጥሩ ነበር። ይህ ሁሉ የሆነው እነሱ ጠርገው በደለደሉት የጦርነቱ ሜዳ ላይ ነበር ።

እነዚህ ሰላም ጠል አካላት ጆሮ ለሰጣቸው ሁሉ የሀሰት ወሬዎችን በማቀበል፣ ባልተገቡ መረጃዎች ልቦናን በማባበል የሚያህላቸው የለም። በእነሱ እሳቤ ጦርነቱ ለዝንት ዓለም ከቀጠለ ህልውናቸው ያብባል። የመኖር ህልማቸው ይፈታል።

አንዳንድ የውጭ አካላት ዓላማ ደግሞ የሰብአዊነት ድጋፍን በማሳበብ የጦርነቱን ዕድሜ ማራዘም ነው። የተፈጠረውን ግጭት በመከተል በእርዳታ ሰበብ ወደ አገራችን የሚገቡ ተላላኪዎች እሳቱን እያዳፈኑ ባሻቸው ጊዜ ለማንደድ ሰበብ ሲፈጥሩ ቆይተዋል። በእርዳታ ሰበብ እግራቸው ምድራችንን በረገጠ ቁጥርም ከመጡበት ዓላማ በተቃራኒው የመቆማቸው እውነት ‹‹ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ›› ን አስተርቷል።

ይህ ብቻ አይደለም። ‹‹ፖለቲከኞች ነን›› የሚሉና ከጦርነቱ የበዛ ትርፍን የሚሹ አካላትም አጋጣሚውን እንደ መልካም ዕድል ሲጠቀሙበት ቆይተዋል። መንግስትን ‹‹እንቃወማለን›› ባዮቹ ሀይሎች ራሳቸውን በውጭ አገራት ጓዳዎች ወሽቀው በሚረጩት መርዝ ሰላም እንዳይወርድ፣ ጦርነቱ በጥልቀት እንዲቀጥል ሲጥሩ ኖረዋል።

ምላሰ ረጃጅሞቹና ዕንቅልፍ የለሾች በተለይ ለትግራይ ህዝብ ህልውና በማሳያነት የሚያቀርቡት እሴት የለም። ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ መፍትሄ የለሽ ንግግሮችን በመደስኮር ለራሳቸው ዕውቅናን ሲሸልሙ ከርመዋል። እነዚህ ተጽእኖ እንፍጠር ባዮች የውጭ አካላትን ምኞትና ፍላጎት ለማሳካት አበክረው የሚተጉ ናቸው።

እንደ ጋዜጠኛ ማርቲን ፕላውት አይነቶቹ በኢትዮጵያ ላይ ሀሰተኛ ዜናዎችን ሲያሰራጩ ቆይተዋል። ፕላውትን የመሰሉ የውጭ አገራት ተላላኪዎች ጦርነቱን አባብሶ ለማንደድም እንደቤንዚን አቀጣጣዮች ነበሩ። ይህ የቀድሞ የቢቢሲ ዜና ወኪል መረጃዎችን ፈብርኮ በማሰራጨት በኩል የሚያህለው አልነበረም። በሁለት ወገኖች መሀል ተገኝቶ ግጭትን በማባባስ በኩል ጥበቡን ተክኖበታል።

እንዲህ አይነቶቹን የውጭ አገራት ተላላኪዎች በማድነቅ ለጦርነቱ ድምቀት የሚሰጡ ሀይሎች የሚያገኙትን ትርፍ ከማሰብ የዘለለ የረባ ዓላማ የላቸውም። ሰላምን ከማወክ ባሻገር ከሚገኘው የነገ ህልም ላይ ተቀምጠው የነገዋን ትግራይ ያስባሉ። እነሱ ሌሎች በከፈሉት መስዋዕትነት የሚመጣን ሲሳይ በዋዛ ማለፍ ፈጽሞ ፍላጎታቸው አይደለም። የነገን ስልጣን ይናፍቃሉ።

ይህን ክፉ ዓላማ ከዳር ለማድረስ ሌት ተቀን የሚተጉት ሀይሎች ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ሰላም እንዳይኖር፣ እርቅ እንዳይፈጠር ለማድረግ እጃቸው ሰፊና ረጅም ነው። በእነሱ ህልም ውስጥ ይህ ዕውን እንዲሆን ያለመሻታቸው እውነትም የሰሞኑን የሰላም ንግግር በግልጽ ሲቃወሙት ተስተውሏል።

በእነዚህ ጸረ ሰላም ሀይሎች ማንነነት ውስጥ ጠብና ጦርነት፣ ግጭትና መፈናቀል ቤቱን ሰርቷል። ሁሌም በንጹሀን ደም መፍሰስ፤ በእናት አባቶች ሞትና ስደት በአገር ውድመትና ታሪክ መጥፋት ውስጣቸው ይፈካል። ክፉ ዓላማቸው ያብባል።

እኛ ግን ዛሬ በታላቁ የሰላም ጎዳና ላይ ቆመናል። ፍቅርን ለሚሹ፣ ሰላምን ለሚፈልጉ ሁሉ ፈጽሞ ፊታችን አይዞርም፣ እጃችን አይታጠፍም። እነሆ! የሰላም አየርን እንፈልጋለን። የምንከተለው መንገድ የምንጓዝበት አቅጣጫ ሰላምና ፍቅር፣ እርቅና ስምምነት እንዲኖረው እንሻለን።

አሁን የጦርነትን ኮሽታ በእጅጉ ጠልተነዋል። ያለፍንበት መንገድ እሾህና ጋሬጣ የበዛበት ነበርና ልንመለስበት አንወድም። አዎ! መንገዶች ሁሉ ወደሰላም እንዲወስዱን፣ ከእርቅ መንደር እንዲያሳድሩን እንመኛለን።

# “የቤት ግንባታ የልማታችን አካል በመሆኑ የግሉ ሴክተር ትኩረት አድርጎ ሊሰራበት ይገባል”

- ወይዘሮ አዳነች አቤቤ
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ



**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የመኖሪያ ቤት ግንባታ ዋነኛው የከተማዋ የልማት አካል በመሆኑ ከመንግሥት በተጨማሪ የግሉ ሴክተር ትኩረት አድርጎ ሊሰራበት እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ገለጹ።

በአዲስ አበባ አያት 49 በሚባለው አካባቢ በሆሴእ ሪል ስቴት የተገነቡ ከ300 በላይ ቤቶችን የያዘውን የየረር ሆምስ የመኖሪያ መንደር መርቀው ከፍተዋል።

በወቅቱ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ በአዲስ አበባ የቤት ፍላጎትንና አቅርቦትን ለማጣጣም እንዲሁም የከተማዋን ውበት ለመጠበቅ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ ከንቲባዋ ገለፃ፤ ዘመናዊ ቤት ከተማዋን ከማስዋብ ባለፈ የነዋሪውን የአኗኗር ዘይቤ ለማዘመን አይነተኛ መንገድ ነው። የግሉ ዘርፍ በቤቶች ግንባታ ልማት ላይ በብቃት መሳተፉ ለሥራ እድል ፈጠራና ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ዘላቂነት አስፈላጊ ነው።

ከተማ አስተዳደሩ በቤቶች ልማት ላይ ከለሚሳተፉ ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል ያሉት ከንቲባዋ፤ የግሉ ዘርፍ በበኩሉ ግንባታዎችን በፍጥነትና በጥራት በማጠናቀቅ የልማቱ አጋር መሆኑን በቀጣይነትም ሊያረጋግጥ ይገባል ብለዋል።

በሀገራችን አንድን ፕሮጀክት አቅዶና ገንብቶ በፍጥነት ለታለመለት ዓላማ የማዋል ልምዱ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ብቻ ሳይሆን በግሉ ዘርፍም ዘንድ እያደገ መምጣቱ በሆሴዕ ሪል ስቴት የተገነባው የረር ሆምስ የመኖሪያ መንደር አንድ ማሳያ ነው ብለዋል።

በከተማዋ የሚገኙ ለልማት የሚሰጡ መሬቶች አልምቶ በተገቢው ሁኔታ ለተጠቃሚው በፍጥነት ማስረከብ ሁል ጊዜ መለመድ ያለበት ተግባር ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ በሆሴዕ ሪል ስቴት የተገነባው የረር ሆምስ የመኖሪያ መንደር ባለፉት ሁለት ዓመታት የነበረው ችግር ሳይገድበው በታቀደለት ጊዜ መጠናቀቁ ሊበረታታና ለሌሎች ተሞክሮ የሚሆን ተግባር ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የሆሴእ ሪል ስቴት ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ሰይፈ ፈቃደ በበኩላቸው፤ የረር ሆምስ የመኖሪያ መንደር፣ በ23 ሺህ ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ መሆኑን ገልጸዋል።

የረር ሆምስ መንደር 280 ባለ አንድ፣ ባለ ሁለትና ባለ ሶስት መኝታ የመኖሪያ ቤቶችንና 10 ሱቆችን፣ 14 የአፓርታማ ህንጻዎችን እንዲሁም 20 ቪላዎችን ያካተተ ነው ብለዋል።

በግንባታ ሂደቱ ከ10 በላይ ኮንትራክተሮች በማሳተፍ ከ500 በላይ ለሚደርሱ ባለሙያዎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን አቶ ሰይፈ አስረድተዋል።

የረር ሆምስ የመሪያና መንደር የግንባታ ሥራው በሀለት ዓመት ከ6 ወር መጠናቀቁ ተገልጿል።

# “የመንግሥት ተቋማትን ወደ ግል ማዞሩ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው”

**- የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ**

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- የመንግሥት ተቋማትን ሙሉ ለሙሉ ሆነ በከፊል ወደግል ማዞር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ አለው ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ ገለጹ።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመንግሥት ይዞታዎችን ወደግል ማዞር እራሱን የቻለ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ አለው። የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል፤ ተወዳዳሪ ተቋም መገንባትም ያስችላል፡፡

መንግሥት የግሉ ዘርፍ ሊሰራበት የሚችልበትን ዕድል እያስፋፋ መሄድ ይኖርበታል ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ይህንን ሃሳብ የሚያጠናክሩ ውሳኔዎችን በቴሌኮምና በፋይናንስ ጉዳዮች ላይ እያከናወነ መሆኑ የሚበረታታ መሆኑን ጠቁመዋል።

መንግሥት በግሉ ዘርፍ ሊሸፈኑ በሚችሉ የስራ መስኮች ሁሉ መሰማራት የለበትም ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ ይልቁንስ መንግሥት የግሉ ዘርፍ ሊሰማራባቸው ባይችልባቸው መስኮች በመሰማራት ውጤታማ ተግባር መስራት ይቻላል ብለዋል፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ መንግሥት ድርጅቶችን እዚህም እዚያም ለብቻው ሲይዝ ለዘረፋ የመጋለጥ ዕድል ይሰፋል። በማሳያነትም በተወካዮች ምክር ቤት ላይ በቀረበ ሪፖርት ከአንድ ሴክተር ብቻ 13 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ብር ነው መዘረፉ መገለጹን አንስተዋል።

የግል ሴክተሩ ሲሳተፍ ግን ብድር ሳይሆን ገቢ ነው የሚኖረው፤ ምዝበራውም ይቀንሳል። በመሆኑም መንግሥት የመቆጣጠር ሥልጣኑን ይዞ የግሉን ዘርፍ ማጠናከር አለበት። የሌሎች አገራት ተሞክሮም የሚያሳየው ይህንኑ መሆኑን ገልጸዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ በምሰራበት ወቅት ናይጀሪያ ውስጥም ቴሌን ወደ ግል ለማዞር ክርክር ነበረባቸው፤ በኋላ አማክረን አሳምነናቸው ገቡበት። አሁን ላይ ከዘርፉ 19 ቢሊዮን ዶላር ድረስ እያገኙ ነው ብለዋል።

ከዚህ መነሻነት የልማት ድርጅቶችን ወደ ግል ኢንቨስትመንት ለውጭውም ኢንቨስትር መለቀቁ አዋጭ ነው። ይህንን አሰራር ሀገር መሸጥ የሚሉ አካላትም ጉዳዩን ካለማወቅ የሚመጣ የተዛባ አስተሳሰብ ነው ሲሉ ባለሙያው ተናግረዋል።

የግሉ ዘርፍ ወደ አገር ውስጥ ሲመጣ ሀብት ይዞ ነው የሚመጣው፤ ዘርፉንም ለማሳደር የሚረዳ አሰራርና ባለሙያ ጭምር ይበልጥ ስለሚያሳትፍ ከሀገር ውስጥ ባለሀብቱ ጋር አጣጥሞ መሄድ እንደሚገባ ጠቁመዋል።

በተመሳሳይም መሬትን በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባ ላይ መሬትን ከተማ ላይ ወደግል ቢዞር አለበት ብለው ያነሱትን ሃሳብ እንደባለሙያ የምደግፈው ሃሳብ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ብቻ ነች መሬትን በመንግሥት ይዞታ ስር አድርጋ የቆየችው ያሉት ባለሙያው፤ መሬት የግል ሲሆን በውጤታማነት ሀብት ለማፍሰስ ያግዛል። አንድ ግለሰብ የራሴ መሬት ነው ብሎ ሲያስብ እዚያ ቦታ ላይ አስተማማኝ ኢንቨስትመንት ለማድረግ ይነሳሳል፤ ቋሚ ንብረት ለማፍራት መተማመኛ ያገኛል ብለዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ የመሬት አስተዳደር ስሪት በራሱ በየአካባቢው ይለያያል በሰሜንና በደቡብ ያለውና በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያለው የመሬት ባለቤትነት ስሪት ለየቅል ነው፡፡

ወጥነት ባለው መልኩ ሰፋ ባለ ጥናት የግሉ ዘርፍ መሬትን በመያዝ እንዴት በስፋት ሊጠቀምበት ይችላል የሚል የመሬት ፖሊሲም ያስፈልጋል ሲሉ ምክረ ሃሳብ አቅርበዋል።

የሌሎች አገራትን ልምድ በመውሰድ መሬት ለትክክለኛው አገራዊ ጠቀሜታ ላለው ልማት ለማዋል ከመንግሥት ወደ ግሉ ዘርፍ መተላለፍ አለበት የሚለው ያስማማል ነገር ግን እንዴት ባለ መልኩ አገራዊ የመሬት ፖሊሲ ስሪት ያስፈልጋል የሚለው ደግሞ ተከታታይ ስራ የሚጠይቅ ነው ብለዋል።

እንደአጠቃላይ ግን የቴሌኮም ዘርፉን፣ የፋይናንስና ኢኮኖሚ እንዲሁም የትራንስፖርትና ሌሎች ኢንቨስትመንቶች ላይ የመንግሥትን ይዞታ ወደ ግል ለማዞር የሚኬድበት አግባብ ኢኮኖሚው ጠንካራ እንዲሆን የሚያግዝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

መንግሥት የኢትዮቴሌኮምን 40 በመቶ ድርሻ ወደ ግል ለማዛወር የዓለም አቀፍ ጨረታ ማውጣቱ የሚታወስ ነው። በተጨማሪ የባንክ አገልግሎቱን ለውጭ አገራት ተቋማት ክፍት እንደሚያደርግም አሳውቋል።

# ኢትዮጵያ ተለዋዋጭ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሁኔታ ውስጥ እንደሚያጋጥምም አስገንዝበዋል፡፡

እንደ አቶ ኃይለማርያም ገለጻ ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ እውን እንዳይሆን ብሎም ኢትዮጵያ እንደ አገር እንዳትቀጥል በአገሪቱ ላይ የተደረገው የውጭ ጫና እንደ ቀላል የሚታይ አይደለም፤ ዳሩ ግን ይህ ጫና ትልቅ ትምህርት የተወሰደበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

የሰሜን የአገሪቱ ክፍል የተከሰተውን ግጭት ተከትሎ ኢትዮጵያን የገጠማት የዲፕሎማሲ ጫና ሊቢያ፣ ሶሪያ፣ ኢራቅ እና ሌሎች አገራት ያፈረሰው ጫና እንደማይተናነስ የጠቆሙት አቶ ኃይለማርያም፤ የኢትዮጵያ ጉዳይ በሃያላን አገራት መካከል መነታረክንና መከፋፈል የታየው ዝም ብሎ ሳይሆን በተሰራው ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

በዓለም ነባራዊ ሁኔታ ለኢትዮጵያ ብሎም ለመላው አፍሪካ የሚያስፈልገው የፉክክር ሳይሆን የትብብር ዲፕሎማሲ መሆኑን ያወሱት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ከዚህ አንጻር በተለይ ኢትዮጵያ ከመደበኛው የዲፕሎማሲ ሥራዋ በተጨማሪ በአፍሪካ ብሎም በዓለም በታዋቂና ተጽእኖ ፈጣሪ ዜጎቿ አማካይነት የጠንካራ ዲፕሎማሲ ሥራ መሥራት እንደሚጠበቅባት መክረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ካላት የመልከዓ ምድር አቀማመጥ እና እድገቷን ከማይሹ ጠላቶቿ የሚወረወሩባት ፍላጻ ለመታደግ የተጀመረው ጠንካራ የጸጥታ ሃይል ግንባታ አንዱ የዲፕሎማሲ ገጽታ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል፡፡

# ለመጀመሪያ ጊዜ ሶስት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የፋብሪካው ባለቤት አቶ አንማው አለሙ ፤ የታሸገ ውሃ መካከለኛው ምስራቅ በተለይም ወደ ሳውዲ አረቢያ ለመላክ ዝግጅት አድርገናል ብለዋል። በ24ሺህ ካሬ ሜትር ላይ የተገነባው ፋብሪካ በሮቦቲክ ቴክኖሎጂ 24 ሰዓት የሚሰራ መሆኑን ገልጸው፤ ፋብሪካው በሰዓት 48 ሺህ ሊትር የታሸገ ውሃ እንደሚያመርት ተናግረዋል።

ለ420 ሰራተኞች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል የፈጠረው ፋብሪካ የታሸገ ውሃን ለውጭ ገበያ በማቅረብ ለአገራችን የውጭ ምንዛሬ ለማስገባት ዝግጅት አጠናቀናል ሲሉም ተናግረዋል።

እንደ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የታሸገ ውሃ ፋብሪካዎች ለ46 ሺህ ዜጎች በቀጥታ እንዲሁም በተጨማሪነት ለ78 ሺህ ሰዎች በተዘዋዋሪ መንገድ የስራ ዕድል መፍጠር ችለዋል።

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# "ኤርታኔጆ"– "የምድሪቱ የቁርጥ ቀን መሪ!"

"ርሀብ ባለበት ተስፋ አይኖርም። ህመምና ብቸኝነት ይሰፍናል። ርሀብ ግጭትንና ጽንፈኝነትን ይጎነቁላል። ሰዎች የሚራቡባት ዓለም ሰላም ልትሆን አትችልም።" ይላሉ እንደ ንስር ኃይላቸውን አድሰው ወደ ብራዚል ፖለቲካ በፕሬዚዳንትነት ብቅ ያሉት ሉላ ዳ ሲሊቫ፡፡ በሰራተኛ ማህበራት እየተደገፉ ያለ አብዮት ሚሊየኖችን ከከፋ ድህነት በማውጣት ተጠቃሚ ማድረግ የቻሉ ፕሬዚዳንት በማለትም ያደንቋቸዋል። ሰራተኛውን መደብና መካከለኛ ገቢ ያለውን የሕብረተሰብ ክፍል አንድ ለማድረግ ባቀጣጠሉትና ሉሊዝም የሚል ስያሜ በተሰጠው ስርዓት ስማቸው አብሮ ይነሳል። በብራዚል ታሪክ ከሰራተኛው መደብ የወጡ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት ይሏቸዋል። የዩኒቨርሲቲን ደጅ ያልረገጡና ዲግሪ የሌላቸው፤ ለሁለት ተከታታይ ጊዜ በዴሞክራሲያው ምርጫ የተመረጡ፤ ስልጣናቸውን በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ላሸነፈ መሪ በሰላማዊ መንገድ ያስረከቡ የመጀመሪያው ፕሬዚዳንት እና የሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ፋና ወጊ ሲሉ ያሞካሿቸዋል። ሉላ ኢናሲዎ ዳ ሲልቫን፡፡

በቅርቡ በተካሄደ የብራዚል ምርጫ ወግ አጥባቂውን ቦልሶናሮን በጠባብ ልዩነት አሸንፈው ወደ ስልጣን የተመለሱት የብራዚል ፕሬዚዳንት ሉላ ኢናሲዎ ዳ ሲሊቫ፤ በዓለማችን ካሉ ታዋቂ ሕዝበኞች/populist/፤ ከሜክሲኮው ፕሬዚዳንት አንድሬስ ማኑኤል ሎፔዝ፣ ከአሜሪካው በርኒ ሳንደርስ፣ ከብሪታኒያው ጄርሚ ኮርቢንና ከሌሎቹ ጋር ስማቸው በግንባር ቀደምትነት ይነሳል። ዓለማቀፍ የተራማጆችን ንቅናቄ በማቀጣጠልም ስማቸው ይነሳል። ሉላ ከ2003 እስከ 2011 ዓ.ም፤ ተከታታይ ሁለት ምርጫዎችን በማሸነፍ ብራዚልን መርተዋል። በስምንት ዓመታት ሚሊየኖችን ከድህነት አረንቋ ማውጣት ችለዋል። በ2018 ዓ.ም ዳግም ወደ መሪነት ለመመለስ ሲዘጋጁ ስልጣን ላይ እያሉ ያልተገባ ጥቅም አግኝተዋል በሚል ተጠርጥረው፤ ጥፋተኛ ሆነው ስለተገኙ የ12 ዓመት እስር ተፈረደባቸው። እሳቸው ግን ክሱ ፖለቲካዊና ከፕሬዚዳንታዊ ውድድሩ ለማስወጣት የተሸረበ ሴራ ነው ይላሉ። ከሕዝብ በተሰበሰበ አስተያየት 50 በመቶ የሚሆኑት የቀድሞውን መሪያቸውን ፕሬዚዳንት ሉላን በታሪክ ምርጡ ፕሬዚዳንት ናቸው ሲሉ መስክረውላቸዋል።

ከ20 ዓመታት በፊት ግራ ዘመምና ሕዝበኛ የሆኑት ሉላ ወደ ስልጣን ሲመጡ ለብራዚል ኢፍትሐዊነት የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ ከበርቴዎች፤ ፕሬዚዳንቱ ብራዚልን ወደ ሶሻሊዝም ርዕዮተ አለም ይቀይሯታል፤ የእኛም ነገር ያበቃል የሚል ስጋት አድሮባቸው እንደነበር "ታይም" ያስታውሰናል። ሉላ ኢናሲዎ ዳ ሲሊቫ የላቲን አሜሪካ ሰራተኛ ቤተሰብ እውነተኛ ልጅ ሲሆኑ፤ የብራዚልን የሰራተኛ ፓርቲ ከመሰረቱት የመጀመሪያውም ናቸው። የስራ ማቆም አድማን መርተሀል በሚል ለስር ተዳርገው እንደነበር የታይም መጽሔቱ ማይክል ሞር ያስታውሰናል። ፕሬዚዳንት ሉላ ካልተሳካ ሶስት ፕሬዚዳንታዊ ውድድር በኋላ መጨረሻ ላይ ሲያሸንፉ በመላው ብራዚላዊ ዘንድ የሚታወቅ ብሔራዊ ተክለ ሰብዕና ገንብተው ነበር ይለናል ሞር፤ ወደ ፖለቲካዊ ዓለም የተቀላቀሉት የፋብሪካ ሰራተኞች ኑሯቸውን ለማሸነፍ ምን ያህል እንደሚደክሙና ለድካማቸው ተገቢውን ክፍያ እንደማያገኙ በራሳቸው ስለ አዩት ነው። ችግረኛ ቤተሰባቸውን ለማገዝ ከ5ኛ ክፍል ትምህርታቸውን አቋርጠው በህጻንነታቸው ጫማ ጠራጊ ሊስትሮ ሆነው ሰርተዋል። እድሜያቸው ከፍ ሲል የፋብሪካ ላብ አደር ሆነው ሲሰሩ ባጋጠማቸው አደጋ ትንሽ ጣታቸውን ማጣታቸውን ሞር ይገልጻል።

የልጅነትና የወጣትነት ዘመናቸው በብዙ ውጣውረድና ፈተና የተሞላ ነው። በ25 አመታቸው የ8 ወር ነፍሰ ጡር ባለቤታቸው፤ በተሻለ ሆስፒታል የወሊድ ክትትል እንዲያደርጉ ገንዘብ ስላልነበራቸው የመጀመሪያ ልጃቸውንም ባለቤታቸውን ተነጠቁ።

ለዚህ ነው ወደ ፕሬዚዳንትነት እንደመጡ ዜሮ ርሀብ ወይም ዜሮ ስታርቬሽን አልያም በፖርቱጊዝ ፎሜ ዜሮ ብለው ንቅናቄ ያቀጣጠሉት። በዚህ ንቅናቄ በአስር ሚሊየኖች የሚቆጠሩ ከሰራተኛው መደብ የሆኑ ብራዚላውያንን ከድህነት አረንቋ ማውጣት ችለዋል። ርሀብን በከፍተኛ ደረጃ ማስወገድ፣ የትምህርትና የጤና መሠረተ ልማቶችን በማስፋፋት የድሀ ዜጎችን ሕይወት ቀይረዋል። ታዋቂው ብራዚላዊ ጋዜጠኛ፣ መሐንዲስና የስነ ማህበረሰብ ሰው ኢውክሊዴስ፤"War of Canudos" በሚለው መጽሐፉ፤ በፖርቱጊዝ "ኤርታኔጆ" ወይም "የምድሪቱ የቁርጥ ቀን ልጅ" የሚለው አባባል የፕሬዚዳንት ሉላ ተክለ ሰብዕና ፍንትው አድርጎ ያሳየዋል ይላሉ ደጋፊዎቻቸው።

የሰሜን ምስራቅ ብራዚል ተወላጅ የሆኑት ሉላ፤ የዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ሌት ተቀን ከሚማስኑ ድሀ ገበሬ ወላጆች በ1945 ዓ.ም የተወለዱ ሰባተኛ ልጅ ናቸው። በበርሀማው የፔርናምቡኮ ዞን በሚገኘው መብራትና የቧንቧ ውሀ በሌለው ሁለት ክፍል የአፈር ቤት ነው የተወለዱት። በከፋ ድህነት ያደጉ የእግራቸው ጫማ ያልነበራቸው ያጣ የነጣ ቤተሰብ አባል ሲሆኑ፤ ሉላ እንደተረገዘ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ፤ ወደ ሳውፖሎ የተሰደዱ አባታቸውን ፍለጋ ከእናታቸው ጋር ወደ ሳውፖሎ አቀኑ።

በስምንት ዓመታቸው የመላላክ ስራ አገኙ። በሚያገኟት ገቢ ቤተሰባቸውን መደገፍ ጀመሩ። በዘጠኝ ዓመታቸው ደግሞ በሳውፖሎ ሰፋፊ አውራ ጉዳናዎች ዳርቻ፤ ሊስትሮ በመሆን ተቀጣሪነት ለምኔ አሉ። ሆኖም የሚያገኙት ገቢ የሚያወላዳ ስላልሆነ መልሰው የአንድ የልብስ ንጽህና መስጫ ሱቅ ረዳት ሆነው ተቀጠሩ። በተጣበበችው ጊዜ የ1ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተምረው በማጠናቀቅ፤ በማሽን ቤት ተቀጠሩ። የፕሬዚዳንት ጁሴሊኖ ኩቢትሼክስ ልማታዊ ፖሊሲ በብራዚል ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ መቻሉ ይወሳል።

በሳውፖሎ የሚገኘው የኢንዱስትሪ ዞን እንደ ስካኒያ፣ ቮልስዋገንና ሌሎች ታላላቅ መኪና አምራቾች ስራ ጀመሩ። በዚህ ኢኮኖሚያዊ መነቃቃት እንደ ሉላ ያሉ በርካታ ወጣቶች የስራ ዕድል ተፈጠረላቸው። ሉላም የብረታብረት ሰራተኛ ሆነው ተቀጠሩ። በ1964 ዓ.ም ወታደራዊ መፈንቅለ መንግስት ተደርጎ የስርዓት ለውጥ በመደረጉ ተነቃቅቶ የነበረው ኢኮኖሚ መልሶ ተቀዛቀዘ። ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተገደቡ፣ ቅድመ ምርመራ ስራ ላይ ዋለ፣ በሰራተኛው ላይ ይፈጸሙ የነበሩ በደሎች ተስፋፉ። የዋጋ ግሽበት ተባባሰ። ብዙዎች ስራ አጥ ሆኑ።

በስማቸው የተሰየመው የምርምር ተቋም፤ ሉላ ከትንሿና በርሀማዋ ፐርናምቡኮ መንደር በህጻንነታቸው ወጥቶ ሳውፖሎ ሲገባ መልመድ ተቸግሮ ነበር ሲል ያስታውሳል። ብዙም ሳይቆዩ ከታላቅ ወንድሞቻቸው አንደኛው፤ በህቡዕ ከሚንቀሳቀስ የኮሚኒስት ህዋስ ጋር ያስተዋውቃቸዋል። በህዋሱ ስብሰባ በሚያደርጉት ተሳትፎ በሰራተኛው ላይ የሚፈጸመው በደል ተቋማዊና መዋቅራዊ መሆኑን በደንብ ይገነዘባሉ።

ሰራተኛው በቂ ክፍያ እንደማያገኝ፣ የመደራጀት፣ የመደራደር መብት፣ የስራ ዋስትናና የስራ ላይ ደህነት ዋስትና እንደሌለው ያጤናሉ። በህቡዕ በሚንቀሳቀሰው የሰራተኛ ማህበር በሚያሳዩት ንቁ ተሳትፎ የስራ አመራር ኮሚቴው አባል ሆነው ተመረጡ። ብዙም ሳይቆዩ በ1969 ዓ.ም የሰራተኛ ማህበሩ መሪ ሆነው ጉብ አሉ ይለናል ኢንስቲትዩቶ ሉላን፤ የሰራተኛ ማህበር መሪ መሆናቸው ህይወትን ፈታኝ ቢያደርግባቸውም፤ ወላጅ እናታቸው ዱና ሊንዱ ነገ የተሻለ ይሆናል አይዞህ እያሉ ያበረታቷቸው ነበር።

የሰራተኛው መብትና ጥቅም ተሟጋች ሉላ በ23 ዓመታቸው ትዳር ቢመሰርቱም፤ ከሁለት ዓመት በኋላ፤ በጉበትና በሳንባ ምች የተነሳና በቂ ህክምና ባለማግኘት ከእርግዝና ጋር ተያይዞ በተፈጠረ ችግር ባለቤታቸውንና ጽንሱን በሞት ተነጠቁ። መሪር ሀዘኑ ከፈጠረባቸው ጭንቀት ለመሸሽ በሰራተኛ ማህበሩና በግል ስራቸው ላይ መጠመድን በጀ ብለው ተያያዙት። ከዚህ በኋላ የትዳሩም የፍቅሩም ነገር ሊሰምርላቸው አልቻለም። ሆኖም በሰራተኛ ማህበሩ ያላቸው ተሰሚነትና ተቀባይነት እያደገ መጣ።

በ1973 ዓ.ም ገና 30ኛ አመታቸውን ሳይደፍኑ የአገሪቱ የሰራተኛ ማህበር ኮንፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ። በ1970ዎች አጋማሽ የሰራተኞች ጥያቄ ከረርና ጠንከር እያለ ሲመጣ ወታደራዊው አገዛዝ በዛው ልክ በኃይል ለማፈን ተንቀሳቀሰ። ፈላጭ ቆራጩ ወታደራዊ አገዛዝ ሁሉንም ተቃውሞዎች ለመጨፍለቅ የተለያዩ የአፈና ስልቶችን መጠቀምን በጀ ብሎ ተያያዘው። ከተማሪዎች ንቅናቄ እስከ የትጥቅ ትግል አመጾችን ያለ ልዩነት በጠመንጃ ለማፈን ይንቀሳቀስ ጀመር። የተመረጡ መሪዎች ፖለቲካዊ መብቶች ሳይቀሩ ተገደቡ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ዕግድ ተጣለ። የሰራተኛ ማህበራት ንቅናቄ ግን ለወታደራዊ አገዛዙ የራስ ምታት መሆኑ ቀጠለ። የፖለቲካ ምህዳሩ እየጠበበ ሲመጣ፤ የግራ ዘመም አቀንቃኞች ሳይቀሩ ማህበሩን በስፋት ይቀላቀሉት ያዙ። ቤተ ክሪስቲያናትና የተማሪዎች ማህበራት እንዲሁ ሰራተኛ ማህበሩን መደገፍ ጀመሩ።

ይሄን አጋጣሚ ወደ አዲስ ምዕራፍ ለማሸጋገር ሉላ በ1978 እና 1980 ዓ.ም አገር አቀፍ የስራ ማቆም አድማ ጠሩ። አድማው ከተገመተውና ከተጠበቀው በላይ መላ ብራዚልን ዳር እስከ ዳር ከመናጡ ባሻገር የሉላንና የፓርቲውን መሠረት አጸናው። በወርሀ ሚያዚያ 1980 ዓ.ም የስራ ማቆም አድማውን በማስተባበርና በመምራት ተጠርጥረው ለ31 ቀናት ታሰሩ። ከእስር እንደተለቀቁ የፖለቲካ ፓርቲ በማቋቋም ወታደራዊ አገዛዙን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ መቃወሙን ተያያዙት። ሉላ ያቋቋሙት የፖለቲካ ፓርቲ በብራዚል ታሪክ ትልቁ ተጽዕኖ ፈጣሪ ከመሆኑ ባሻገር ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመመለስ በሚደረገው ጥረት ግንባር ቀደም ሆነ። በሰራተኛው መደብ አስኳልነት የተመሠረተ ቢሆንም ልሒቃን፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ አርቲስቶች፣ ተማሪዎችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች በስፋት ይቀላቀሉት ያዙ።

ሉላ ዳ ሲልቫ የብራዚልን ፖለቲካዊ መልክዓ የቀያየረው ፓርቲ የመጀመሪያ ፕሬዚዳንት ሲሆኑ፤ ከሰራተኛው ድምጽነት ወደ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪነት ተሸጋገሩ። በብራዚል የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሒደት ዛሬ ድረስ በአርሾነት ስማቸው በሰፊው ይወሳል። የፖለቲካ ፓርቲ መስርተው ከወጡ በኋላም በሰራተኛ ማህበራት ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ በማሳደር ይታወቃሉ። በብራዚል የሚገኙ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማስተባበርና በመምራት በ1983 ዓ.ም በአገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚጠይቅ ታላቅ ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ።

ከሶስት ዓመት በኋላ በ1986 ዓ.ም በተካሄደ ምርጫ ለምክር ቤት አባልነት ሲወዳደሩ በታሪክ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ በማያውቅ ከፍተኛ ድምጽ ተመረጡ። ሕገ መንግስታዊ ጉባኤ እንዲካሄድና ማሻሻያዎች እንዲደረጉ፤ የሰብዓዊና የማህበራዊ መብቶች እውቅና እንዲያገኙ፤ የወሊድ ፈቃድ አራት ወራት እንዲሆን፤ የስራ ሰዓት በሳምንት ከ48 ወደ 44 ሰዓታት ዝቅ እንዲል ብርቱ ትግል አድርገዋል። ከ29 ዓመታት በኋላ በተካሄደ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለፕሬዚዳንትነት ተወዳድረው በጠባብ የድምጽ ልዩነት ተሸንፈዋል።

በ1990 ዓ.ም የዜግነት ተቋምን በመምራት ለአገርና ለዜጋ የሚጠቅሙ የፖሊሲ ሀሳቦችን ከማመንጨታቸው ባሻገር፤ ብራዚልን ለስምንት ዓመታት የመሩት ፕሬዚዳንት ፈርናንዶ ኮሎር ላይ ስልጣንን አላግባብ መጠቀም ክስ እንደሚሰረትባቸው የአንበሳውን ድርሻ ተጫውተዋል። በብራዚል የላይኛውም ሆነ የታችኛው ምክር ቤቶች የተስተዋሉ ምዝበራና ሌሎች ብልሹ አሰራሮች ምርመራ እንዲደረግባቸው ሰርተዋል። ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምሮ እድሜ ልካቸውን አንድ ጊዜ ለሰራተኛው በኋላ ደግሞ ለብራዚላውያን ሲታገሉ የኖሩት ሉላ፤ ከሶስት ጊዜ እልህ አስጨራሽ ትግል በኋላ በ2002 ዓ.ም ከፍተኛ ድምጽ በማግኘት የብራዚል ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ። በብራዚል ታሪክ ከሰራተኛው መደብ ወጥተው ፕሬዚዳንት በመሆናቸው አልቮራዶ ቤተ መንግስት ለመጀመሪያ ጊዜ የገቡ ተብለው በታሪክ ተመዘገቡ። ሁለት ተከታታይ ምርጫዎችን በማሸነፍ ስልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ፍትሐዊ የገቢ ክፍፍል እንዲኖር፤

በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ብራዚላውያን የምግብ፣ የህክምና፣ የትምህርትና የብድር አገልግሎት በማቅረብ፤ ሰፊ የስራ ዕድል በመፍጠርና የደመወዝ ማሻሻያ በማድረግ በአስር ሚሊየኖች የሚቆጠሩ ዜጎችን ከከፋ ድህነት ማውጣት ችለዋል። የመኖሪያ ቤት፣ መንገድ፣ የጤናና የትምህርት ተቋማት ግንባታን በማስፋፋት በዜጎች ኑሮ ላይ የሚጨበጥ ለውጥ አምጥተዋል። ፕሬዚዳንት ሉላ ዳ ሲልቫ የስልጣን ዘመናቸውን በ2010 ዓ.ም አጠናቀው፤ ለተመራጯ ፕሬዚዳንት ዴልማ ሮሴፍ ሲያስረክቡ 87 በመቶ በሚሆኑ ብራዚላውያን ዘንድ ያለ ልዩነት አድናቆት ተቸሯቸዋል። በሉላ የስልጣን ዘመን በአገሪቱ ታሪክ ከድህነት ወለል በታች የነበሩ በርካታ ዜጎች ከድህነት የተላቀቁበትና ሰፊ የስራ ዕድል የተፈጠረበት ሆኖ ተመዝግቧል።

መስከረም 22 ቀን ብራዚል በምታደርገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ሉይዝ ኢናሲዎ ሉላ ዳ ሲሊቫ እንደ ንስር ኃይሌን አድሼ ተመልሻለሁ ሲሉ ደጋፊዎቻቸውን አስፈነደቁ። ግራ ዘመሙ ሉላና ስልጣን ላይ የነበሩትና ቀኝ አክራሪውና የላቲኑ ትራምፕ የሚል ቅጽል የተሰጣቸው ሀየር ቦልሶናሮ ለፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ተፋጠጡ። ሉላ ለስምንት አመታት ፕሬዚዳንት እያለሁ ብራዚል ለዜጎቿ ከዛሬው የተሻለች ነበረች። አሁን ኢፍትሐዊነት ሰፍኗል።

በተለይ ዝቅተኛው የሕብረተሰብ ክፍልና ሰራተኛው በገዛ አገሩ ጥቂቶች ሲበለጽጉ እሱ የበይ ተመልካች ሆኗል። ብመረጥ ይሄን ኢፍትሐዊ የሆነውንና ለጥቂቶች ብቻ የቆመውን አድሎአዊ ስርዓት ለመላ ብራዚላዊ በእኩልነትና በፍትሐዊነት በሚያገለግል እተካዋለሁ አሉ። ከ2019 ዓ.ም ጀምሮ ስልጣን ላይ የነበሩትን ፕሬዚዳንት ሀየር ቦልሶናሮ ግን ለባለጠጋዎች የቆሙና ጸረ ዴሞክራሲ ናቸው ሲሉ ይከሷቸዋል። ቦልሶናሮ በበኩላቸው ሉላ አክራሪ ሶሻሊስትና ጸረ ነጻ ገበያ ስለሆነ አገሪቱን ወደ መቀመቅ ያወርዳታል። ከዚህ አደጋ ብራዚልን የምታደጋትና ብልጽግናዋን የማስቀጥለው እኔ ነኝ በማለት መራጮችን ቀሰቀሱ። ሆኖም ሉላ በመጀመሪያ ዙር ተቀናቃኛቸውን በጠባብ ልዩነት ቢመሩም ከ50 በመቶ በላይ ድምጽ ባለማግኘታቸው ለ2ኛ ዙር ተወዳድረው ዳግም በጠባብ ልዩነት አሸንፈው የብራዚል ፕሬዚዳንት ሆኑ። ደጋፊዎቻቸው አደባባይ በመውጣት ደስታቸውን በእንባ እየተራጩ ገለጹ። አማዞንም ወዳጇ ሉላ ስለተመረጡላት ሳያረግድ ይቀራል።

ፈጣሪ ሰላማችንን ያጽናልን ! አሜን ።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ሕገርና ህዝብን ማገልገል ክብር ነው!

እፀገነት አክሊሉ

"አገልጋይነት ታላቅነት ነው። ክብር የሚገኘው ከማገልገል ነው። ፈጣሪን፣ አገርን፣ ሕዝብን፣ ከማገልገል ውጭ ምን ሕይወት አለ። ሁላችንም በአንድ ቦታ አገልጋዮች በሌላም ቦታ ተገልጋዮች ነን። አገልጋይነት የሁላችንም ባህልና ሥነ ምግባር ከሆነ የትኛውም መስሪያ ቤት መልካም አስተዳደር የሰፈነበት ይሆናል። የሆኑ አካላት ብቻ እንዲያገለግሉን ከጠበቅን ግን በአንዳንድ ቦታዎች ተፈልጎ የሚገኝ ብርቅ ሀብት ይሆንብናል። በቂና ብቁ አገልጋዮች የሌሏት አገር፣ በዕድገት መራቅና መምጠቅ ይቸግራታል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ናቸው።

አዎ ለገባው ወይም ለተገነዘበው ሰው አገልጋይነት ውድና ትልቅ ስጦታ ነው። ሰው በተሰጠው የስራ ድርሻ ሁሉ ሰዎችን ማገልገል መቻል አለበት። ይህንን በማድረጉ ደግሞ ከሚያገኘው ወይም ከሚሰማው የመንፈስ እርካታ በተጨማሪ አገሩ ትኮራበታለች፤ ህዝቡ በማገልገሉም የሚሰጠው ምስጋና በቀላሉ የሚታይም አይደለም።

የዛሬ የሕይወት ገጽታ አምድ እንግዳችን አገርና ህዝብን ከማገልገል በላይ ክብር የለም ይሉናል አቶ ሰለሞን ተስፋዬ።

አቶ ሰለሞን ተስፋዬ ተወልደው ያደጉት በአዲስ አበባ ከተማ መስፍን ሐረር መንገድ ወይም አዲሱ ገበያ አካባቢ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውንም በዳግማዊ ሚኒሊክ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት መከታተላቸውን ይናገራሉ።

"......አባቴ በልጅነቴ ነው የሞተብኝ እኔም ያደኩት ከእናቴ እናት ከአያቴ ጋር ነበር፤ ያው የአያት ልጅ እንደሚባለው በሚችሉት አቅም በጥሩ ሁኔታ አሳድገውኛል። ትምህርቴንም በአግባቡ እንድማር አግዘውኛል። ሆኖም እኔም ትምህርቴን ሳልጨርስ አያቴ የህይወት ጥሪ ደርሷቸው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ከእናቴ ጋር መኖር ጀመርኩ" ይላሉ።

አቶ ሰለሞን ረዳት የሌላቸው እናታቸው ጋር ሲሄዱ ዝም ብለው ተማሪ ሆነው ብቻ አይደለም የቀጠሉት ይልቁንም በእናት ከሚገናኙት ወንድማቸው ጋር በመሆን የተለያዩ ስራዎችን በመስራት እናታቸውን እየደገፉ ትምህርታቸውንም እየተከታተሉ ለትንሽ ጊዜም አጎታቸው ጋር እየተቀመጡ ኑሮን ተያያዙት እንጂ።

እየሰሩ መማር ለአቶ ሰለሞን ከባድ ቢሆንም በትምህርታቸው ግን ቀልድን አያውቁም ነበርና ትምህርታቸውን በአግባቡ እየተከታተሉ በደረጃም እየወጡ ነበር ሲማሩ የነበሩት።"......የትምህርት መጀመሪያዬ የቄስ ትምህርት ስለነበር ዘመናዊ ትምህርት ቤት ስገባ ብዙ አልተቸገርኩም፤ እንደውም ብዙ አገዘኝ እንጂ፤ በዚህ ምክንይት ደግሞ አንደኛና ሁለተኛ ነበር የምወጣው በመምህራኖቼም የምወደድ ተማሪ ነበርኩ" በማለት ስለራሳቸው ይናገራሉ።

በዚህ ሁኔታ እየተማሩ 12ተኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ለመውሰድ የግድ ከእናታቸው ጋር የኑሮን ጫና መተጋገዝ ስለነበረባቸው እሳቸው እየሰሩ መማሩን አላቋረጡም። በዚህ ላይ ደግሞ የደርግ መንግስት ቀይ ሽብር በሚል ምክንያት ብዙ ወጣቶችን ይገድል የነበረበት ጊዜ ስለነበር አስፈሪ ጊዜ እንደሆነ ይናገራሉ።

"......በወቅቱ የኑሮ ችግር ብቻ ሳይሆን ይገጥመን የነበረው ወታደራዊው ደርግ ወጣቶችን በገፍ እያፈሰ ጦር ሜዳ የሚልክበት እንዲሁም ቀይ ሽብር በማለት የሚረሸንበት ጊዜ ነበር። ብዙ ጓደኞቼም አገር ጥለው ከመሰደድ ጀምሮ ሕይወታቸውንም ያጡ ነበሩ፤ እኔም ገና የ12ተኛ ክፍል ተማሪ ብሆንም ከችግሩ ለማምለጥ ስል ብቻ በተማሪነት እድሜዬ ስራ ለዚያውም የመንግስት ስራን ማፈላለግ ጀመርኩ" ይላሉ።

አቶ ሰለሞን የመንግስት ሰራተኝነትን የሚገልጽ መታወቂያ ይዘው ወቅቱን ለማምለጥ ብዙ ጥረት በማድረግ በመጨረሻም በ1971 ዓ.ም አርቲስቲክ ማተሚያ



ፎቶ : ፀሐይ ንጉሴ

**አቶ ሰለሞን ተስፋዬ**

ቤት የሚባለው መስሪያ ቤት በጸሀፊነት የስራ መደብ በ55 ብር የወር ደመወዝ መቀጠራቸውን ይናገራሉ።

".....ያኔ የመንግስት ሰራተኝነት መታወቂያ የያዘ ሰው ይከበራል፤ ኸረ እሱ ስራ አለው ይባልለታል፤ በተመደብኩበት የስራ መስክ ላይ እጅግ ደስተኛ ሆኜ እሰራ ስለነበር እንዲሁም የማሳየውም የስራ ተነሳሽነት ጥሩ ስለሆነ በዓመቱ የደመወዝ እድገት አግኝቼ ነበር" ይላሉ።

አሁን የ 12ተኛ ክፍል ትምህርታቸውን አጠናቀዋል እናም ስራ መቀየር ፈለጉና ስራ ሲያፈላልጉ በቀድሞ አጠራሩ ጭማድ በኋላም ኢጭማኮ የሚባለው መስሪያ ቤት ተወዳድረው በማለፋቸው በጸሀፊነት የስራ መደብ ከፍ ባለ ደመወዝ ተቀጠሩ፤ አሁን የስራ አካባቢው መቀየሩ የደመወዝ እድገቱ አስደሰታቸው እናታቸውንም በደንብ ለመደገፍ ስላስቻላቸው በሞራል ስራቸውን መስራት ቀጠሉ።

"........ከዛን ጊዜ ጀምሮ ለእኔ አገርና ህዝብን እንደማገልገል ትልቅ ነገር አለ ብዬ አላምንም ነበርና ስራዬን ላቅ ባለ ትጋት መስራት ከትልቅ ትንሹ ጋር በተግባቦት መዋል ደግሞ የሕይወት መርሄ ስለነበር በስራ ላይ የከፋ ችግር ሳይገጥመኝ ለ 17 ዓመታት ያህል አገለገልኩ" ይላሉ።

ከጸሀፊነት ጀምረው እስከ ሂሳብ ሹምነት ድረስ ያሉ የስራ ኃላፊነቶችን ሁሉ በብቃትና በጥሩ የስራ ስነስርዓት የከወኑት አቶ ሰለሞን እግረ መንገዳቸውን የከፍተኛ ትምህርታቸውን እየተማሩ ዲግሪያቸውን ለመያዝ በቁ።

ሕይወት ሁሌም አዲስ ነገር ትፈልጋለች መኖር ካለ ለውጥ ይናፍቃል ለውጡ ደግሞ በደረጃም በደመወዝም ሲሆን ሙሉ ይሆናል የሚሉት አቶ ሰለሞን እሳቸውም 17 ዓመት ከሰሩበት ኢጭማኮ ለውጥን በመፈለግ ወደ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን በሂሳብና በጀት የስራ መደብ ላይ ለመስራት ተቀጠሩ።

በድንገት እናታቸውን ለመርዳት እየረዱም ለመማር የገቡበት የስራው ዓለም እንዲህ እንዲህ እያለ እዚ ሲያደርሳቸው አቶ ሰለሞንም ለስራ የሚሰጡት ዋጋ ከፍ እያለ በኑሯቸውም ለውጥ እያመጡ ህዝብና አገርን የማገልገል ጽኑ ፍላጎታቸው እያደር እየዳበረ ሲመጣም ይሰማቸው ነበር። በዚህም ምክንያትም በፌደራል ከተሞች ልማት ኢንስቲትዩት በኦዲት መምሪያ ኃላፊነት። በስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በበጀት ዝግጅትና ክትትል ዋና ክፍል ኃላፊነት። በፌደራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን በኦዲት መምሪያ ኃላፊነት ። በጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር የባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት ኃላፊነት የስራ መደቦች ላይ እየተመደቡ ተቋምንም አገርንም የሚጠቅም አስተዋጽዖ አበርክተዋል።

አቶ ሰለሞን ይህ ማህበራዊ ተሳትፏቸው ብሎም በስራ ላይ የሚያሳዩት ትጋትና የስራ ፍቅር በአካባቢያቸው ነዋሪዎች ዘንድ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤትን እንዲቀላቀሉ ምክንይት ሆናቸው።

".....ህዝብን ማገልገል መታደል ነው እኔም በሰፈሬ አካባቢ የማሳየው ትጋት በበጎ ፍቃድ የምሰራቸው ስራዎች እንዲሁም በተለያዩ የስራ መስኮች ላይ ተሰማርቼ ስሰራ በነበረኝ የስራ አፈጻጸም ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት ገብቼ ድምጽ እንድሆናቸው ጠየቁኝ እኔም ፍቃደኛ ሆኜ ተወዳድሬ በማሸነፍ በ2000 ዓ.ም ምክር ቤቱን በመቀላቀል ለአምስት ዓመታት ያህል የመረጠኝን ህዝብ ሳገለግል ቆየሁ "በማለት ይናገራሉ።

አቶ ሰለሞን የአምስት ዓመት የምክር ቤቱን አገልግሎታቸውን ቢጨርሱም ህዝቡ ግን ይሻለናል በማለቱ ምክንያት በ2005 ዓ.ም እንደገና ተመርጠው ገቡ።

ሆኖም አቶ ሰለሞን ከልጅነታቸው ጀምሮ ህልማቸው የነበረው ነገር አገልጋይነት የሚለው ስሜት ነውና ብዙ መስሪያ ቤቶች እየተዘዋወሩ ቢሰሩም ያን ያህል ግን በሚፈልጉት ልክ ማገልገል የቻሉ አይመስላቸውም። አቶ ሰለሞን ከመንግስት የስራ ኃላፊነታቸው ባሻገር ያለቻቸውን ትርፍ ሰዓት በአግባቡ በመጠቀም በሚኖሩበት አካባቢ ያሉ የህብረት ስራዎችን በመስራት ማህበረሰብን ማገልገል የተመሰከረላቸው ሚናቸውም ነው። ነገር ግን ከትልቁ ህዝብን የማገልገል ህልማቸው እንዳይቀሩ አንድ ጥሩ አጋጣሚ ተፈጠረላቸው፤ እሱም በምክር ቤት አባል እያሉ የራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል ዋና ስራ አስኪያጅ ሆነው ተሾሙ። አቶ ሰለሞን ይህንን እድል በቀላል አላዩትም ይልቁንም አገርና ህዝብ የሚማረርበትን የመንግስት የህክምና ተቋም አገልግሎት ላቅ ወዳለ ደረጃ አሸጋግረው ተምሳሌት ማድረግን ተመኙ እንጂ ።

ኃላፊነታቸውን ተቀብለውም ከፍ ባለ የስራ ትጋትና ያለመሰልቸት ብዙ ስራዎችን ማከናወን ጀመሩ፤ በዚህም በሆስፒታሉ ላይ የሚጠብቁትን አይነት ለውጥም የማየት እድሉን እያገኙ ሲመጡ ይበልጥ ለስራው ተነሳሱ። አሁን ሃሳባቸውም ስራቸውም ሆስፒታሉን መለወጥ ላይ ብቻ ሆነ፤ በዚህም ስራቸው ከህክምና ባለሙያዎች እስከ ታካሚዎች ድረስ ጥሩ ግንኙነትን በመፍጠር ችግሮችን እለት በእለት እንዲፈቱና እልባት እንዲያገኙ በማድረግ የማይናቅ ሚናን ተወጡ።

"......ራስ ደስታ ሆስፒታል በስራ አስኪያጅነት ስመደብ በጣም ነበር ደስ ያለኝ። በውስጤ ያለውን የማገልገል ፍላጎትና ፍቅር ላምወጣበት የምችልበት ብቸኛ ተቋምም እንደሚሆን አስብ ነበር። በዚህም ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ በሆስፒታሉ ውስጥ ጎደሉ የምላቸውን ነገሮች ሁሉ ለማሟላት ከፍ ያለ ጥረት ሳደርግ ህዝቡ ምን ዓይነት ህክምና አገኘ፤ ምን ጎደለው፤ የሚለውን ስከታተል ችግር በተፈጠረበት አካባቢም የመድፈን ስራ ስሰራ ነበር የምውለው በዚህም በጣም ደስተኛ ነበርኩ" በማለት የሆስፒታል ትዝታቸውን ይናገራሉ።

".....ራስ ደስታ ሆስፒታል በከተማው ካሉ አጠቃላይ ሆስፒታሎች አንዱና ትልቁ ነው። ሆስፒታሉ ከገባሁ በኋላ ብዙ ስራ ነበር የጠበቀኝ። በተለይም ወቅቱ የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (ቢፒአር) የተካሄደበት ስለነበር ሰራተኛውን ማረጋጋት ስራዎችን ለተገቢው ሰው መስጠት ይገባ ነበርና ይህንን ሁሉ ማቀናጀቱ ጊዜ ከመውሰዱም በላይ ስራውን ከባድ አድርጎት ነበር" ይላሉ።

ሆስፒታሉ ውስጥ ዶክተሮች ነርሶት እንዲሁም የአስተዳደር ሰራተኞች ስለሆኑ ያሉት እነዚህን በአንድ አቀናጅቶ መምራቱ ደግሞ ምናልባትም እውቀት የስራ ልምድ እንዲሁም ከፍ ያለ ተነሳሽነትን የሚጠየቅ ነበርና አቶ ሰለሞን እነዚህ አስታርቀው ሰውና ስራን በእኩል ለመምራት ከፍ ያለ ጥረትንም አድርገዋል።

"......ልክ ጠዋት በስራ ገበታዬ ላይ ስገኝ የመጀመሪያ የማደርገው ታካሚዎች ጋር ሄዶ መጎብኘት ምን ዓይነት አገልግሎት አገኛችሁ? አዳራችሁ እንዴት ነበር? ምን ዓይነት ችግር ገጠማችሁ? አሁን ምን እንዲደረግላችሁ ትፈልጋላችሁ? የሚያስፈልገውን መድሃኒት አግኝታችኋል ወይ? ዶክተሮችና ነርሶች ጎብኝተዋል ወይ? የሚለውን በመጠየቅ ምልሻቸው ማስታወሻዬ ላይ መዝግቤ ቢሮ በመግባት በተሰጡት አስተያየቶች ላይ ሜዲካል ዳይሬክተሩን ጠርቼ እናወራበታለን፤ እነዚህ በዚህ ይሻሻሉ የሚል የስራ መመሪያ እሰጣለሁ፤ በዚህ ሁኔታ ስናልፍ ደግሞ ችግሮች እየቀነሱ ስራዎች እየተስተካከሉ ታካሚዎች በሚያገኙት አገልግሎት እየረኩ ዶክተሮችና ነርሶችም በስራቸው ደስተኛ እየሆኑ ሄዱ፤ በሆስፒታሉ ውስጥ ያሉ የስራ ክፍሎችም በዚህ ሁኔታ በመደራጀታቸው አሁን ለተጠያቂነት ራሱ የሚመች ምህዳር ተፈጠረ " በማለት ሁኔታውን ያስታውሳሉ።

### የግል ህክምና መስጫ ማዕከል አጀማመር

በመንግስት ሆስፒታሎች ውስጥ ከስራ ሰዓት ውጪ የግል ህክምና መስጫ ተቋማት እንዲከፈቱ የሚያዘው መመሪያ ወጣ ። የዚህ መመሪያ መዘጋጀት ዋና አላማው ሀኪሞች በመንግስት ሆስፒታል ተቀጥረው ሲሰሩ የሚከፈላቸው ክፍያ በቂ ስላይደለ ከስራ ገበታቸው ላይ የመጥፋት አንዳንዴም ጨርሶ የመቅረት ሁኔታ ስለሚያሳዩ ያንን ነገር ለማስቀረት ነበር። አንድ ታካሚ ሆስፒታል መጥቶ በመረጠው ሐኪም እንዲታከም ማስቻል ሌላው ነው። ሆስፒታሎች በዚህ ሁኔታ አገልግሎት ሰጥተው በሚገኘው ገቢ ሆስፒታሉን ማስፋፋት የሚጎሉትን ነገሮች ማሟላት ከአላማዎቹ የሚጠቀሱ ናቸው።

እነዚህን ዓላማዎች ያነገበው የግል ህክምና መስጫ ማዕከል ምስረታ አስፈሪ ሆነ፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ጤና ቢሮ ስርም ሆነ በፌደራል ጤና ሚኒስቴር የሚመሩ ሆስፒታሎች አገልግሎቱን ማስጀመር ፈሩ፤ መመሪያውን ታቅፎ ተፋጦ መቀመጥ እጣ ፋንታው ሆነ።

".......ይህንን የህክምና ማዕከል ምስረታ ሁሉም ሆስፒታሎች መጀመሩን ቢያምኑበትም ደፍሮ ወደ ስራ ማስገባት ላይ ግን ከፍ ያለ ፍርሃት ነገሰ፤ በዚህ መካከልም የሚጀምረው አጥቶ መመሪያው ከወጣ በኋላ እንኳን ወራቶች ተቆጠሩ፤ እኔ ግን ማኔጅመንቱን ሰብስቤ እጃችን ላይ መመሪያ ደንብ አለ ወደተግባር ለመግባት የያዘን ነገር ምንድነው? ስል ጠየኳቸው፤ የእነሱ ምላሽ ተሞክሮ ከየት እናመጣለን የሚል ነበር " ይላሉ።

አቶ ሰለሞን በአስፈላጊነቱ ላይ ከፍ ያለ እምነት

**ማህበራዊ**

# የሕይወት ገጽታ



ስላደረባቸው ተሞክሮ ከየት ማግኘት እንደሚቻል ማፈላለግ ጀመሩ። በአዲስ አበባ ደረጃ ይህንን አገልግሎት የጀመረ ሆስፒታል ባይኖርም ኦሮሚያ ክልል ጤና ቢሮ በቢሾፍቱ ከተማ ሆስፒታል ላይ አገልግሎቱን መጀመሩን ሰሙ። ይህንን ጊዜ የስራ ባልደረቦቻቸውን ይዘው ወደስፍራው አቀኑ።

"......ወደ ቢሾፍቱ ሆስፒታል ሄደን እንዴት ጀመራችሁት? በስራው ላይ ምን ምን ዓይነት ውጤት እንዲሁም ችግር ገጠማችሁ? በማለት ተወያየን፤ በዚህም ጥሩ ልምድ በማግኘታችን ወደራሳችን ተቋም መጥተን ኮሚቴ አዋቀርን፤ ከዚህ በተጨማሪም የህክምና መስጫ ቦታ የዶክተሮች የነርሶች ቢሮዎች የድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች ዝግጅት አደረግን፤" ይላሉ።

ነገር ግን ወደ ስራ ለመግባት ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ አልነበረም እንደውም ዶክተሮቹ ቅሬታ አቀረቡ፡፡ ይኸውም እኛ በትርፍ ጊዜያችን ሌሎች ቦታዎች እየሰራን ነው፤ ይህ ደግሞ ገና ሰውም አያውቀውም፤ ዝም ብለን እዚህ መቀመጥ አንችልም አሉ። አቶ ሰለሞን ግን ለዚህም ችግር መፍትሔ አላጡም ብዙ አስበው አንድ ድምዳሜ ላይ ደረሱ።

"......በሁሉም ሆስፒታሎች ላይ የድንገተኛ ክፍልና አስተኝቶ ማከም ላይ አንድ አንድ ሀኪሞች በትርፍ ጊዜ ክፍያ ያድራሉ፤ በመሆኑም እነዚህ ሀኪሞች የትርፍ ጊዜ ክፍያቸውም ሳይቀር በግል ህክምና ተቋሙም የሚያገኙት ክፍያ እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሰሩስ ስል ከማኔጅመንቱ ጋት ተወያየንና መስማማት ላይ ደረስን፤ እነሱም ሁለት ጥቅም የሚያገኙበት በመሆኑ በደስታ ስራውን አስጀመሩት" በማለት አጀማመሩን ይናገራሉ።

አቶ ሰለሞን ልክ ዶክተሮቹ ፍቃዳቸውን ሰጥተዋቸው ስራው እንደተጀመረ እርሳቸው ደግሞ የራሳቸውን ስራ መስራት ያዙ፤ እሱም ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል ከቀኑ 10 ሰዓት ጀምሮ በግል ህክምና መስጫ ማዕከሉ

> *አገርና ህዝብን ማገልገል የዘወትር ፍላጎታቸው የህይወትም መመሪያቸው የሆነው አቶ ሰለሞን በሆስፒታላቸው ውስጥ ብዙሀኑን ሊጠቅም ሊያገለግል ብሎም የብዙ ሰው ችግር ሆኖ የሚያስተውሉትን የዐይን ህክምና እጦት በራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል እውን ለማድረግ ስራዎችን መስራት ጀመሩ*

መታከም ለሚፈልጉ ተገልጋዮች አገልግሎት መስጠት መጀመሩን የሚገልጽ ማስታወቂያ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን አስነገሩ። በአንድ ወር ውስጥ በታካሚ ተጥለቀለቀ ሆስፒታሉም ሰው በዛ ብሎ ስራዎች እንዳይበላሹ ወይንም ደግሞ ከደረጃው ዝቅ እንዳይል ከፍ ያለ ክትትል ያደርግ ጀመር።

አሁን አቶ ሰለሞን ሌላ የተገቢነት ጥያቄ እንዳይነሳባቸው ቀዳዳዎችን ለመድፈን ፈለጉ "..... መጀመሪያ አገልግሎቱ ይጀመር ሲባለ ዶክተሮቹ ከግል ስራችን ያደናቅፈናል ብለው በማቅማማታቸው በትርፍ ሰዓት ክፍያቸው ላይ ተደርቦ እየተከፈላቸው እንዲሰሩ ነበር ያደረኩት፤ ነገር ግን ስራው ከተለመደና የታካሚው ቁጥር እየጨመረ ከመጣ በኋላ ሁሉም በዚህ መንገድ ማለፍ ፈለገ ግን ደግሞ ሁለት ክፍያ መክፈል በህግ ተገቢነት ስለማይኖረው ኮሚቴ በማቋቋም ለሀኪሞችም ለነርሶችም ተራ እንዲወጣ አዘዝኩ በዛ መሰረትም ስራውን መስራት የጀመረ፤" ይላሉ።

አገልግሎቱ ሲጀመር 70/30 የሚባል ክፍያ እንደነበረው የሚናገሩት አቶ ሰለሞን ይህም ማለት በስራው ከሚገኘው ገቢ ሀኪሞቹና ነርሶች 70 በመቶ ተካፋይ ሲሆኑ 15 በመቶው ለተቋሙ ማስፋፊያ። 15 በመቶ ደግሞ ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች እንዲሆን ነው የተደረገው። ይህ አሰራር ደግሞ ተጨማሪ ገቢን ያስገኘ በመሆኑ ሁሉም በስራው ላይ ለመሳተፍ እንዲወስኑ እንዳደረጋቸው ይናገራሉ።

".......ሰው እየጨመረ ሲሄድ ገቢም ይጨምራል በዚህ እኔም ሆንኩ የማኔጅመንት አባላቱ በሁኔታው በጣም ደስተኞች ነበርን። ከምንም በላይ ደግሞ ሌሎች ሆስፒታሎች እኛን አይተው አገልግሎቱን ለመጀመር በብዛት ይመጡ የነበረ መሆኑ ከምንም በላይ አስደሳች ነበር ሁሉም የመንግስት ሆስፒታሎች የራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል የግል ህክምና መስጫ ተቋምን ተሞክሮ ቀምሮ ነው ዛሬ ላይ አገልግሎቱን በስፋት እየሰጡ ያሉት"ይላሉ።

በሌላ በኩልም ወደ ሆስፒታሉ ገቢ የሚሆነውን 15 በመቶ ገንዘብ በተለይም የመድሃኒት እጥረት ሲያጋጥም። የላብራቶሪ ማሽኖች እክል ሲገጥማቸው እንዲሁም የላብራቶሪ ሳምፕሎችን ለመመርመር የሚያግዙ ኬሚካሎች ሲያልቁ ማሟያና ማስጠገኛ እየዋለ ክፍ ያለ ጥቅምን ያስገኝ ጀመረ።

### በሆስፒታሉ የዐይን ህክምን እንዲጀመር

አገርና ህዝብን ማገልገል የዘወትር ፍላጎታቸው የህይወትም መመሪያቸው የሆነው አቶ ሰለሞን በሆስፒታላቸው ውስጥ ብዙሀኑን ሊጠቅም ሊያገለግል ብሎም የብዙ ሰው ችግር ሆኖ የሚያስተውሉትን የዐይን ህክምና እጦት በራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል እውን ለማድረግ ስራዎችን መስራት ጀመሩ። በዚህም ከኮሪያ የመጡና ቪዥን ኬር የሚባል የህክምና ቡድን በሆስፒታሉ ውስጥ ቦታ ከተሰጠው ምንም አይነት ክፍያ ሳይጠይቅ የዐይን ህክምናን በነጻ እንደሚሰጥ ገለጸላቸው። ይህ ሁኔታ ደግሞ እሳቸውም ለህዝባቸው የሚመኙት አገልግሎት ነበርና ከማኔጅመንት አባላት ጋር በመወያየት በግቢው ውስጥ የነበረውን በተለይም የህክምና ባለሙያዎቹ ጊዜ ሲኖራቸው እንዲያነቡ ለማድረግ የተዘጋጀ ክፍል ትርፍ ክፍል የነበረው በመሆኑ ለህዝቡ የሚሰጡትን ጥቅም ታሳቢ በማድረግ ቢሮው እንዲሰጣቸው ሆነ።

"......እነዚህ የዐይን ህክምና ባለሙያዎች የዶክተር የነርስ ወጪዎችን ራሳቸው ሸፍነው መድሃኒት ራሳቸው አቅርበው ነው አገልግሎቱን የሚሰጡት፤ በዚህም ብዙ ሰዎች ተጠቅመውበታል፤ እስከ አሁንም በሆስፒታሉ ውስጥ አገልግሎት እየሰጡ ለብዙሀኑም ብርሃን እየሆኑ ነው"።

እነዚህ ባለሙያዎች ራዕያቸው ከፍ ያለ ነበር በሆስፒታሉ ውስጥ በምስራቅ አፍሪካ ብቸኛ የዐይን ክሊኒክና ማስተማሪያ ሊከፍቱ ፍቃዳችንን ጠይቀውን ነበር፤ ማኔጅመንቱም ኮሪያ ድረስ ሄዶ ልምድ ቀምሮ የመምጣት እድልም አግኝቷል። በራሳቸው ወጪ ፕላን አሰርተው ነበር፤ በመጨረሻም ለግንባታ ቦታውን የሚፈቅድላቸው አካል አጥተው እስከ ዛሬ ድረስ ስራው በእንጥልጥል ቀርቷል። እኔም ይህ ነገር በጣም ይቆጨኛል ይላሉ።

አቶ ሰለሞን በዚህ መልኩ ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታልን አንድ እርምጃ ያራምዱት እንጂ በቦታው ላይ ለመቆየት አልተፈቀደላቸውም፤ ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክር ቤት በመግባት የመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኑ። እዛ እያገለገሉም ሳሉ ኦዲት ላይ ብዙ አገልግሎት ስላላቸው ለስራችን ያግዘናል በማለት ወደ አዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር ቢሮ ምክትል ኃላፊ በመሆኑ እንዲዘዋወሩ ሆነ።

አቶ ሰለሞን ህዝብና አገርን ማገልገል መታደል ነው በሚለው የህይወት መርሃቸው ያለፉትን 41 ዓመታት በመንግስት መስሪያ ቤት አገልግለዋል፤ በዚህም በርካታ የስራ ኃላፊነቶችን በአግባቡ ከመወጣታቸውም በላይ ብዙ ባለሙያዎችን አፍርተዋል፤ በዚህ አገልግሎታቸውም ህዝብና አገር ኮርቶባቸዋል።

አቶ ሰለሞን በተለይም ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታል ላይ በሰሩት ስራ እርካታ ይሰማቸዋል ነገር ግን የዐይን ህክምናና የስልጠና ማዕከሉን እውን ሳያደርጉ መቅረታቸው ያስቆጫቸዋል፤ በሌላ በኩልም የከተማው ህዝብ ከእለት እለት ቁጥሩ በእጥፍ እየጨመረ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ያሉት የጤና ተቋማት እየተመጣጠኑ አይደለም፤ ይህ ብቻም ሳይሆን ከነዋሪው ባልተናነሰ ከተለያዩ ክልሎች ለተሻለ ህክምና ወደከተማዋ የሚገባው ህዝብ ቀላል የሚባል አይደለም። በመሆኑም ሆስፒታሎቻችን የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ይወጡ ዘንድ ስር ነቀል የሆነ የለውጥ ስራና የማስፋፊያ ግንባታዎች ያስፈልጓቸዋል በማለት ይናገራሉ።

ለምሳሌ ራስ ደስታ ዳምጠው ሆስፒታልን ለማስፋፋት ሙከራዎች ነበሩ ከኋላው ያሉ ነዋሪዎችን ምትክ በመስጠት አስነስቶ ግንባታም ለማከናወን እቅድ ነበር፤ የከተማ አስተዳደሩም ፈቅዶ እስከ አፈር ምርመራ ድረስ የደረሰ ስራም ተከናውኗል፤ ነገር ግን ቁርጠኝነት በማጣት ምክንያት እስከ አሁን ድረስ ግንባታው አልተጀመረም። ይህ ደግሞ ሆስፒታሉ ለአካባቢው ሰዎችና አገልግሎቱን ለሚፈልጉ አካላት በሙሉ ተገቢውን አገልግሎት በመስጠት ላይ ክፍተቶች እንዲኖሩበት ስለመሆኑም ይጠቅሳሉ።

"......ጤና ሚኒስቴር ዘርፉን ለማሳደግ አገልግሎቱንም ተደራሽ ለማድረግ እያደረገ ያለው ጥረት እጅግ ጥሩና የሚበረታታ ቢሆንም አሁንም ግን ብዙ የሚቀሩን ስራዎች አሉ፤ በሆስፒታል ደረጃ የጤና ተቋማት ቁጥር መብዛት አለባቸው። ቁጥር ብቻ ሳይሆን በተቻለ መጠንም ጊዜውን የዋጀ የህክምና መሳሪያ ማሟላት ላይም ከፍተኛ ትኩረት ተደርጎ መሰራት አለበት" ይላሉ።

### መልዕክት

ስራ የሚባለው ነገር የሁላችንንም ስብዕና የሚወስን ነው። አንድ ሰው ከቤቱ ሲወጣ ለስራ ነው የምሄደው ብሎ ማመን ይኖርበታል። በስራ ገበታው ላይ ተገኝቶ የሚጠበቅበትን ለማከናወን ጊዜውን አቅሙን በአግባቡ መጠቀም ያስፈልጋል። እኔ ስራን የጀመርኩት ገና በልጅነት እድሜዬ ነው። ከዛን ጊዜ ጀምሮም አሁን እስካለሁበት ደረጃ ድረስ የሰራኋቸውን ስራዎች በሙሉ ወድጄ በሙሉ ልቤ ጊዜዬን ሰጥቼ አገሬን ማገልገል አለብኝ ብዬ ለራሴ ቃል ገብቼ ስለሰራሁ በጣም ደስተኛ ነኝ።

ስራ ከጠሉት የሚጠላ ነገር ነው ወጣቶች ዛሬ ላይ ስራ ይጀምሩና ገና ዓመት ሳይሞላቸው ስለ ስራው ማማረር። በሚከፈላቸው የወር ደመወዝ ደስተኛ አለመሆን ያመጣሉ፤ ይህ ግን ተገቢ አይደለም፤ ሌላው ዓለም "ለእናት አገሬ በነጻ ብሰራስ" ብሎ አገልግሎት የሚሰጥ ትውልድ ማፍራት ችሏል፤ ምናልባት እኛ ያንን ለማድረግ ገና ልንሆን እንችላለን ነገር ግን ባለንበት ደረጃም ቢሆን ስራችንን አክብረን የአገልጋይነት ስሜት ተሰምቶን በታማኝነት ኃላፊነታችንን ከተወጣን እድገት ገንዘብ የሚገኙና የሚመጡ ናቸው። ዋናው ነገር ስራውን መውደድ ነው።

### የቤተሰብ ሁኔታ

አቶ ሰለሞን የተሰጣቸውን ኃላፊነት ብቃት ከመወጣት ስራ ከመውደድ ባሻገርም ቤተሰብ መስርተው ሁለት ልጆችን ወልደዋል፤ አሁን ላይ አያት ለመሆን በቅተዋል። ለልጆቻቸውም እሳቸው ያለፉበትን የስራ ሂደት በማስተማር የአገር ፍቅር ኖሯቸው የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ የሚያስችሉ ትምህርቶችን ከአባትነት ጋር አዋህደው በመስጠት እዚህ ደርሰዋል።

# የዝነኞች ገጽ

# ደምሴ ዳምጤ

**አቤል ገ/ኪዳን**

የዓለም ዋንጫ ዛሬ በኳታር ዋና መዲና ዶሀ ይጀመራል። ለቀጣይ አንድ ወርም የዓለም አይኖች ወደ መካከለኛው ምስራቋ አገር ይዞራሉ። የዓለም መገናኛ ብዙሃንም ዋና ትኩረታቸውን ወደዚያ ይሆናል። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሀንም እንደዚያው። ስለ ኢትዮጵያ የስፖርት ሚዲያ ስናወራ ደግሞ በምንም መልኩ ሊዘነጋ የማይችለው ሰው ታላቁ ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ነው። እኛም የዓለም ዋንጫውን አስታከን ይህን ታላቅ ጋዜጠኛ ልንዘክረው ወደድን።

ደምሴ ዳምጤ የተወለደው በ1945 ዓ.ም ሲሆን እድገቱም በምስራቃዊቷ ሞቃታማ ከተማ ድሬዳዋ ነው። ብዙዎች እንደሚናገሩለት ደምሴ ገና ከልጅነቱ ለስፖርት የተሰጠ ነበር። ነገር ግን ለስፖርት ተወዳዳሪነት ሳይሆን ለስፖርት ዘገባ። አፍላው ደምሴ ተሰጥኦውን ፈልጎ ለማግኘት ጊዜ አላባከነም ነበር። የስፖርት ዘጋቢነት ሙያውን የመረጠው ገና በልጅነቱ ነው። በድሬዳዋ ከተማ አሸዋማ ስፍራዎች ላይ ይደረጉ የነበሩ የታዳጊ ህጻናትና የወጣቶች የእግር ኳስ ግጥሚያዎች ደምሴ ወደ ስፖርት ዘጋቢነት ሙያ እንዲገባ ትልቅ ሚና ነበራቸው። ደምሴ የኳስ ፍቅር ነበረው። የኳስ ፍቅሩን በንቁ ተመልካችነት፣ በታዛቢነትና በደጋፊነት ከመግለጽ ባለፈ በተጨዋችነት ታቅፎ የተሳተፈበት የእግር ኳስ ቡድን አልነበረም። የእርሱ ትኩረትና ሕልም መጫወት ላይ አልነበረም፤ መዘገብ ላይ እንጂ።

ተዘራ እሸቴ የተባሉ የደምሴ የቅርብ ወዳጅ ስለደምሴ በጻፉት ጹሑፍ ደምሴ ወደ አማተር የጋዜጠኝነት ስራ የገባበትን አጋጣሚ እንዲህ ይገልጹታል፡-

« ... በወቅቱ የነበሩት የድሬዳዋ ስፖርት ኮሚቴ አባላት የስራና የቤተሰብ ኃላፊነት ጫና የነበረባቸው ሰዎች ነበሩ። በዚህም የተነሳ የስፖርት ዘገባውን አጠናቅሮ ለዜና የማብቃት ድክመት ጎልቶ ይታይባቸው ነበር። በዚህ ክፍተት ነበር ደምሴ የሕይወት ጥሪውን ለማሳካት ብቅ ያለው። ሕልሙን እውን ለማድረግ የነጻ አገልግሎት ለመስጠት ራሱን አቀረበ። አዎንታዊ ምላሽም አገኘ። በሙያው መደበኛ ስልጠና ሳይኖረው ትምህርቱንና የስፖርት ዘጋቢነቱን አጣምሮ ያዘ። በእርሱ የእድሜ ክልል የነበሩት እኩዮቹ ባልሄዱበት ጎዳና ጉዞውን ቀጠለ። ነፃ የስልክ አገልግሎትና ነፃ የስታዲየም መግቢያ ካርድ ተሰጥቶት አገልግሎት መስጠት ጀመረ። በጥረቱም ስኬታማ ሆነ ... የድሬዳዋ ስፖርት አፍቃሪዎችንም ቀልብ መግዛት ቻለ። ደምሴን በየመንገዱ እየጠራ አድናቆቱን የሚቸረው የድሬዳዋ ስፖርት አፍቃሪም በረከተ። ስሙ ገነነ። ወደፊት ጎልቶ የሚወጣ የጋዜጠኝነት ሙያ ችሎታ እንዳለውና ለሙያውም የተሰጠ መሆኑንም አሳየ። በጊዜውም «አማተር ጋዜጠኛ» ተባለ። በዚህ ወቅት ያጎለበተው ልምድና እውቅና ለኋለኛው የጋዜጠኝነት ዘመኑ የማዕዘን ድንጋይ ሆኖለት አለፈ ...» ብለዋል።

በወቅቱ የደምሴ ዘገባ በእግር ኳስ ተመልካቹ ዘንድ ተወዳጅነትን ቢያተርፍለትም በተጫዋቾች እና አሰልጣኞች ዘንድ ግን አልተወደደለትም ነበር። ምክንያቱም ደምሴ ጨዋታውን ምስል ከሳች ለማድረግ የሚጠቀማቸው ቃላት የተጫዋቾችን ድክመት የሚያሳዩ ስለነበሩ ነው። አጥቂው በረኛውን እንዴት እንዳለፈው ሲናገር አጥቂው ቢደሰትም በረኛው ግን ያኮርፍ ነበር። እንዲህ እንዲህ እያለ በደምሴ ዘገባ በበጎ ያልተነሱ ተጫዋቾች ደምሴን ያኮርፉትና መንገድ ላይ ሲያገኙትም ይተናኮሉት ነበር። ከሁሉም በላይ ግን ዘገባው በድሬደዋው ተመልካች እና አዲስ አበባ ባሉ አንጋፋ ጋዜጠኞች አይን ውስጥ ከተተው።

ደምሴ አማተርነትን ተሻግሮ ዋና/መደበኛ/ ጋዜጠኛ የሆነበት አጋጣሚ ከ10ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ጋር የተያያዘ ነው። ወቅቱ ኢትዮጵያ 10ኛው የአፍሪካ ዋንጫን የምታስተናግድበት ጊዜ ነበር። ጋዜጠኛ ሰለሞን



ተሰማና ባልደረባው ይንበርበሩ ምትኬ የተወሰኑትን ጨዋታዎች ተከታትለው ለመዘገብ ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ ገብተዋል። የአጋጣሚ ነገር ሆነና ደምሴ ከባድ ትኩሳት የተቀላቀለበት ጉንፋን ያመውና ሲጠብቀው ከነበረው ታላቅ ጨዋታ ቀርቶ ቤት ውስጥ ይውላል። ቀልቡን ከሰረቁት እውቅ ጋዜጠኞች ጋርም ሳይታደም ይቀራል። ሰለሞንና ይንበርበሩም ከጨዋታው ፍጻሜ በኋላ የሙያ ባልደረባቸውን ለመጠየቅ አድራሻውን ያጠያይቃሉ። የደምሴንና የተዘራን ቅርበት ከሚያውቁ ሰዎች በተደረገ ጥቆማ ተዘራ እንደሚፈለግ ከስታዲየሙ የድምጽ ማጉያ ሰማ። የደምሴ ጉዳይ እንደሆነ ፈጥኖ የተረዳው ወዳጁ ተዘራ በተባለው ቦታ ፈጥኖ ተገኘ። ከዚያም በቀረበላቸው መኪና ተያይዘው ወደ ደምሴ መኖሪያ ቤት (ወደ ታላቅ እህቱ ቤት) አመሩ። ታላቅ እህቱ ከባለቤቷና ከሦስት ልጆቿ እንዲሁም ከደምሴ ጋር የሚኖሩባት አንዲት ክፍል ቤት ሲደርሱም ሰለሞንና ይንበርበሩ ባዩት ነገር እጅግ ተገረሙ፤ ተደናገጡ። ሰለሞን « ... እንደዚህ አልጠበኩም ነበር ...» ሲል ይንበርበሩም ፊቱን አቀጭሞ የእርሱም ስሜት ተመሳሳይ መሆኑን ገለፀ። ደምሴ ለብዙ ጊዜያት በነፃ ሲያገለግል የቆየው በአስቸጋሪ ህይወት ውስጥ ሆኖ እንደነበር እነ ሰለሞን ተረዱ።

ወደ መኪናቸው ሲመለሱም ደምሴ የሚኖረው ከማን ጋር እንደሆነ ተዘራን ጠየቁት። ተዘራም ከታላቅ እህቱ ቤተሰብ ጋር እንደሆነ ተናገረ። ደምሴ ራሱን ከሱስ ጠብቆ ከአባቱ ከምትደረግለት ድጎማ ላይ ቆጥቦ፤ አለባበሱን አሳምሮ መታየቱ ጥሩ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች ልጅ እንደሆነ ሳያስጠረጥረው አልቀረም።

እነ ሰለሞንም ባዩት ሁኔታ ውስጣቸው ተረብሾና ግምታቸው ከእውነታው ጋር ተጋጭቶባቸው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ። በዚያን ሰሞን አንድ የስፖርት ጋዜጠኛ ከአገር ወጥቶ አልተመለሰም ነበር። እነ ሰለሞንም አዲስ አበባ እንደተመለሱ የደምሴን ጉዳይ ቅድሚያ ሰጥተው ያዙት። በወቅቱ የነበሩት የስራ ኃላፊም ከአገር ወጥቶ ባልተመለሰው ጋዜጠኛ ቦታ ሌላ አማተር ጋዜጠኛ ለመቅጠር ዝግጅት አጠናቀው ጨርሰዋል። በዚህ ጊዜ ነበር እነኚህ ተደማጭነት የነበራቸው እውቅ ጋዜጠኞች ደምሴ ለዓመታት በነፃ ሲያገለግል በአስቸጋሪ ህይወት ውስጥ ሆኖ እንደነበር አለቃቸውን አስረድተው ያሳመኑትና ሀሳቡንም እንዲቀለብስ የተማፀኑት።

እነ ሰለሞንም ደምሴ በአስቸኳይ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ ነገሩት። ደምሴም በፍጥነት ወደ አዲስ አበባ ሄደ፤ ከአማተር ጋዜጠኛነት ወደ መደበኛ/ዋና/ ጋዜጠኛነት ተሸጋገረ። ጋዜጠኝነትም ሙያው ሆነ። በርቀት ሲያደንቃቸው ከነበሩት ጋዜጠኞች ጋርም በቅርብ ሆኖ ደመወዝ ተከፍሎት ለመስራት በቃ። እነ ሰለሞንም ፈለጋቸውን ሲከተል የነበረውን ደምሴን እጁን ይዘው ከደረሱበት አደረሱት። ደምሴም በሙያውም አንቱ ተባለበት። ከኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ከስፖርት አፍቃሪው የኅብረተሰብ ክፍልም አድናቆትንና ተወዳጅነትን አተረፈበት።

በደምሴ የጋዜጠኝነት ታሪክ ተጠቃሹ ቀን ታህሳስ 17 ቀን 1980 ዓ.ም ነው። እለቱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ከዙምባቡዌ አቻው ጋር በምስራቅ እና መካከለኛው አፍሪካ ዋንጫ ፍፃሜ የሚጫወትበት ቀን ነበር። ከአዲስ አበባ ስታዲየም ጨዋታውን ቀጥታ በኢትዮጵያ ሬዲዮ ደምሴ ዳምጤ ሲያስተላልፍ የተጠቀማቸው ቃላት አይረሴ ናቸው። በተለይ የዙምባቡዌ ብሔራዊ ቡድን 1ለ0 እየመራ ሳለ ያደረጋቸው ገለጻዎች ደምሴ ለአገሩ እና ለእግር ኳስ ያለው ፍቅር ፍንትው ብሎ የታየበት ነበር። እስኪ ከዚያ ዘገባ የተወሰነውን እናስታውስ..

"... አማኑኤል አሁን ... አማኑኤል ለሙሉዓለም ... ሙሉዓለም ለመንግሥቱ ሁሴን ... መንግሥቱ ሁሴን ለአማኑኤል ... አሻማ ... ሙሉዓለም አሁን አሻማ ... አሻ ... አሻማ ... ሙሉዓለም አሻማ ... በጭንቅላት ወይኔ ... ወይኔ ... ወይኔ ገብሬ ... ገብሬ የመታውን ... የዙምባቡዌው 2 ቁጥር... በራሱ ግብ ላይ ... በራሱ ግብ ላይ ከመረብ አሳረፈ ... በራሱ ግብ ላይ ከመረብ አሳረፈ ... ፤ ... አሁን 1ለ1 ካለቀ ሦላሳ ደቂቃ ይጨመራል፤ ሰዓቱ አልቆ ነበር"

በተጨማሪው 30 ደቂቃ የውጤት ለውጥ ባለመኖሩ አሸናፊውን ለመለየት ሁለቱ ቡድኖች ወደመለያ ምት አመሩ። ደምሴ ዳምጤ ሲቃ እየተናነቀው አስራ ሁለቱን መለያ ምቶች እንዲህ እያለ ማስተላለፍ ቀጠለ፡-

፩. "... ሰባት ቁጥሩ ነው የሚመታው ... የታወቀው የክንፍ አጥቂያቸው .... አሁን ሰባት ቁጥሩ ሄዷል ... ተካበ ቦታውን ይዟል ... ሰባት ቁጥሩ ኳሷን አስቀምጦ የዳኛ ውሳኔ በመጠበቅ ላይ ነው ... ምታ ብለውታል ... መታ ... ተካበ አዳነ ...ተካበ የመጀመሪያውን አድኗል ...

ተካበ የመጀመሪያውን አድኗል ... ግሩም ነው! ተካበ የመጀመሪያውን አድኗል ... ግን ቁርጡ በዚህ አይታወቅም ... ገና ... ነው"

"ነጋሽ አስቀምጧል ... ነጋሽ ሊመታ ነው ... ነጋሽ መታ ... ቀረቀባት ... ቀረቀባት ነጋሽ ... ግሩም ግብ ... ጠረቀማት ... ገብቷል የእኛ ... ጠረቀመው ... ጥሩ ምት ነው! የመታው ነጋሽ ጠረቀመው ... አሁን ተመትቶ እስካላለቀ ቁርጡ አይታወቅም።"

፪. "...የሚመታው 15 ቁጥሩ ነው ... ሁለተኛው ነው ለዙምባቡዌ ... መታ ... ተካበ አዳነ ... ተካበ አሁንም አዳነ ... ጉድ ነው ... ጉድ ነው ... ጉድ ነው፤ ተካበ አሁንም አዳነ ... የሚገርም ነው፤ ሜዳው ተደበላለቀ..."

"... አሁን አማኑኤል ሊመታ ነው ... አማኑኤል ሊመታ ነው ... አማኑኤል ... ሰጠሰጠው ... ሰጠሰጠው ... ሰጠሰጠው ... ምን ዓይነት ግብ ነው ... ምን ዓይነት ግብ ነው ... ምን ዓይነት ግብ ነው ... አሁን 2ለ0 እየመራን ነው ..."

፫. "... ዙምባቡዌ አሁን ሦስተኛውን ሊመታ ነው ... 14 ቁጥሩ ሊመታ ነው ... ጉድ ነው ... መታ ... ገባ"

"... ገብረመድህን ሊመታ ነው ... ምታ አሉት ... መታ ... ወይኔ ... ወይኔ ... ወይኔ ... ግሩም ግብ ገብሬ.."

፬. 10 ቁጥሩ ሊመታ ነው ... 10 ቁጥሩ ሊመታ ነው አሁን ... መታ ... ኸረ ... አስገባ ...ምቱ ይቀጥላል"

"...አሁን በቀለ ካገባ ያልቃል ... በቀለ ካገባ ... በቀለ ካገባ ያልቃል ... ካገባ ... ምታ አሉት ... በቄ መታ ... ወይኔ ውጪ ሰደዳት ... ተነቃንቋል ግብ ጠባቂው ... ተነቃንቋል ... ተነቃንቋል አሉ ግብ ጠባቂው ... ሊደገም ነው ... ውጪ ወጥቶ ነበር ... ግብ ጠባቂው መነቃነቁ በጀን እንጂ ... "

"አይዞህ በቄ ... በቄ አሁን ሊመታ ነው ... መታ ... ውይ ... መለሳት ግብ ጠባቂው ... መለሳት ... መለሳት ... መለሳት ... መለሳት ..."

፭. "8 አሁን ሊመታ ነው ... ምታ አሉት ... አልመታም ... መታ ... ገባ ... ገባ ..."

"...አሁን መንግሥቱ ሁሴን ሊመታ ነው ... መንጌ አሁን ገላግለን ... መንጌ መታ ... መታ ... ወይኔ ወይኔ ... ግብ ጠባቂው መለሰ ..."

፮. "...3 ቁጥሩ ሊመታ ነው ... 3 ቁጥሩ ሊመታ ነው ... ውጪ ... ውጪ ... ውጪ ... ውጪ ... (ደምሴ እንዲህ ይበል እንጂ ተጫዋቹ ገና አልመታም) ... ውጪ ... ውጪ ሰደዳት ..."

"... አሁን ዳኛቸው ነው የሚመታው ... ዳኙ ሊመታ ነው ... ሰው ዝም ቢል ይሻላል ይጨነቃል ... አሁን ግብ ጠባቂው ቦታውን ... ቦታውን ... አሁን ይገላግለናል ... ካገባ ትገላገላለች ... አሁን ዳኙ ሊመታ ነው ... በዙምባብዌ ላይ ... ዳኙ ... ወይኔ ወይኔ ... ጨፈረ ደነሰበት ... ደንሶ አገባ ዳኙ ... ደንሶ አገባ ... በጣም አስደናቂ ግብ ነው ዳኙ ...

... ዳኙ አሁን ደንሶ ጨፍሮ አገባ ... አታለለው ቀኙን አሳይቶ ግራውን ... ግራውን አሳይቶ በቀኙ ... አሁን ተጫዋቾቻችን ደስታቸውን እየገለፁ ነው ... ወደሜዳ ህዝቡ ገባ ... በጣም የሚያስደንቅ ነው አሁን ... ዳኙ ... ተመልካቹ እንደተመኘኋት አገኘኋት ይላል ..."

ከ40 ዓመታት በላይ ያለድካም በቅንነትና በትጋት ያገለገለው አንጋፋው ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ፣ ባደረበት ሕመም ምክንያት ሕክምናውን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ሲከታተል ቆይቶ በ60 ዓመቱ፣ ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ.ም. አርፏል። ሥርዓተ ቀብሩም ወዳጅ ዘመዶቹ፣ ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣናት፣ የስፖርት ቤተሰቦችና አድናቂዎቹ በተገኙበት በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተፈጽሟል። ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ባለትዳርና የሦስት ልጆች አባት ነበር።

# ዓለም አቀፍ

## ኢንተርፖል የአፍሪካ ቁጥር አንድ ባለጸጋዋ እንስት ላይ የእስር ማዘዣ አወጣ

በጋዜጣው ሪፖርተር



የቀድሞ የአንጎላ ፕሬዚዳንት ኤድዋርድ ዶስ ሳንቶስ ልጅ የሆነችው ኢዛቤል ዶስ ሳንቶስ የአፍሪካ ቁጥር አንድ ባለጸጋ እንደሆነች የፎርብስ ሪፖርት ያስረዳል። አንጎላ ከፖርቹጋል ቅኝ ቅዛት ነጻ እንድትወጣ በማድረግ ለረጅም ዓመታት የሀገሪቱ መሪ በመሆን ካገለገሉ በኋላ በምርጫ ከሥልጣን ተነስተዋል።

የቀድሞው የአንጎላ የኮሙኒኬሽን ሚኒስትር በሙስና ክስ 14 ዓመታት እስር ተፈረደባቸው፡፡

ሥልጣን የተቆጣጣረው የወቅቱ የአንጎላ መንግስትም ኤድዋርዶ ዶስ ሳንቶስ ቤተሰብ የሀገሪቱን ሀብት መዝብረዋል በሚል ክስ መስርቷል።

ይሄንን ተከትሎም ዓለም አቀፉ የፖሊስ ተቋም ወይም ኢንተርፖል በአንጎላዊቷ የአፍሪካ ቁጥር አንድ ባለጸጋ እንስት ላይ የእስር ማዘዣ ማውጣቱን ሮይተርስ ዘግቧል። ኢዛቤል ዶስ ሳንቶስ በአሁኑ ወቅት ከአንጎላ ውጪ እንደሚኖሩ የተገለጸ ሲሆን በፖርቹጋል፣ ለንደን ወይም አረብ ኢምሬት ሊኖሩ እንደሚችሉ ተገምቷል።

ኢዛቤል ዶስ ሳንቶስ ከዚህ በፊት ከአንጎላ መንግሥት ስለቀረበባቸው ክስ ከብዙሃን መገናኛዎች ለቀረበባቸው ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ "እኔ ምንም አይነት ሙስና አልፈጸምኩም" ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ኢንተርፖል ከወቅቱ የአንጎላ መንግሥት በቀረበለት ጥያቄ መሰረት በኢዛቤል ሳንቶስ ላይ የእስር ማዘዣ ሊያወጣ እንደቻለ በዘገባው ላይ ተጠቅሷል።

የ49 ዓመቷ ኢዛቤል አባቷ ኤድዋርዶ ሳንቶስ በፕሬዚዳንትነት ሥልጣን ላይ በነበሩበት ወቅት ከባለቤታቸው ጋር በመሆን አንድ ቢሊዮን ዶላር ሙስና ፈጽመዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል።



## አሜሪካ ግዙፍ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኗን ወደ ደቡብ ኮሪያ ላከች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ ቢ -1ቢ የተሰኘውን ግዙፍ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኗን ወደ ደቡብ ኮሪያ ልካለች።

ዋሽንግተን ኤፍ 16 ተዋጊ ጄቶችንም ወደ ሴኡል መላኳ ተሰምቷል። የአሜሪካና ደቡብ ኮሪያ የጦር አውሮፕላኖች የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ተጀምሯል። ሀገራቱ ልምምዱን የፈረጠመ አቅማቸውን ማሳያ አድርገው ይጠቀሙበታል ነው የተባለው።

የሀገራቱ የጋራ ወታደራዊ ማዘዣ ያወጣው መግለጫ እንደሚያሳየው፤ የደቡብ ኮሪያ ኤፍ 35ኤ ጄቶች በአሜሪካ የጦር አውሮፕላኖች ታጅበው ልምምዳቸውን እያደረጉ ነው። በዚህ ልምምድ የሁለቱ ሀገራት ወታደራዊ አቅም በጉልህ ታይቷል፤ ዋሽንግተን የኮሪያ ልሳነምድርን ውጥረት ለማርገብ ቁርጠኝነቷንም አሳይታለች ይላል መግለጫው።

ሀገራቱ የሰሜን ኮሪያን እንቅስቃሴ በቅርበት ለመከታተልና ለፀብ አጫሪ ድርጊቷም ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት መዘጋጀታቸውም ነው በመግለጫው የተነሳው። ሰሜን ኮሪያ ህዋሶንግ 17 የተሰኘውን አህጉር አቋራጭ የባለስቲክ ሚሳኤል በትናንትናው እለት ሞክራለች።

የኒዩክሌር አረር መሸከም የሚችለው ህዋሶንግ እስከ 15 ሺህ ኪሎሜትሮች የመጓዝ አቅም እንዳለው ተነግሯል። የኪም ጆንግ ኡን ሀገር አሜሪካ ጎረቤቶቿን ደቡብ ኮሪያና ጃፓን አጋር ለማድረግ የምታደርገውን እንቅስቃሴ ሚሳኤል በማስወንጨፍ እየገለፀች ነው።

ደቡብ ኮሪያና አሜሪካ የጀመሩትን ወታደራዊ ልምምድ እንደ ጦርነት ሰበቃ የተመለከተችው ፒዮንግያንግ፥ ወደ ጃፓን እና ደቡብ ኮሪያ ሚሳኤል ተኩሳለች። አሜሪካ መድረስ ይችላል የተባለውን አህጉር አቋራጭ ሚሳኤል መሞከር መጀመሯም የኮሪያ ልሳነ ምድርን ውጥረት ይበልጥ ጨምሮታል።

አሜሪካ በቅርቡ ሰሜን ኮሪያ ከሚሳኤል ማስፈራሪያዋ ካልታቀበች ለደቡብ ኮሪያና ጃፓን ኒዩክሌር እስከማስታጠቅ እደርሳለሁ ማለቷ ይታወሳል። ዋሽንግተን የቀጠናው አጋሮቿን በካምቦዲያ ካወያየች በኋላ የመጀመሪያ የሆነው የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ከወደ ፒዮንግያንግ የሚሳኤል ምላሽን እንዳያስከትል ተሰግቷል።

## የጨረታ ማስታወቂያ

የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ በ2014 በጀት ዓመት ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ፡

1ኛ. ለተማሪዎች ምግብ የሚውል የተጋገረ እንጀራ ግዥ፣
2ኛ. ለተማሪዎች ምግብ የሚውል የከብት ስጋ ግዥ፣
3ኛ. ለተማሪዎች ምግብ የሚውል ምስር ክክ ግዥ፣
4ኛ. የድንችና ካሮት ግዥ
5ኛ. የመካኒካል ኬሚካልና ማቴሪያል ኢንጂነሪንግ ት/ቤት ለመማር ማስተማር የሚውሉ ዕቃዎች ግዥ፣
6ኛ. ለሲቪል ኢንጂነሪንግ እና አርክቴክቸር ት/ቤት ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች ግዥ፣
7ኛ. ለኤሌክትሪካል ምህንድስና እና ኮምፒውቲንግ ኢንጂነሪንግ ት/ቤት ለመማር ማስተማር አገልግሎት
የሚውሉ ዕቃዎች ግዥ፣
8ኛ. የአፕላይድ ተፈጥሮ ሳይንስ ት/ቤት ለመማር ማስተማር አገልግሎት የሚውሉ ዕቃዎች ግዥ፣
9ኛ. የፅሕፈት መሳሪያዎች ግዥ
10ኛ. የባር ኮድ ሪደር ግዥ
11ኛ. የሞተር ሳይክል ጥገና ግዥ
12ኛ. የሪኮ ፎቶ ኮፒ ማሽን ጥገና አገልግሎት ግዥ በግልጽ ጨረታ ተጫራቾችን በማወዳደር ግዢ መፈጸም ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚያስችላቸውን ሕጋዊ ሰነዶቻቸውን ከመወዳደሪያ የጨረታ ሰነድ ጋር፣

ሀ/ በዘመኑ የታደሰና በዘርፉ አግባብነት ያለው ህጋዊ የንግድ የሥራ ፍቃድ እና የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣
ለ/ የግብር ከፋይነት ማረጋገጫ ሰርትፊኬት/TIN/፣
ሐ/ የተጨማሪ እሴት ታክስ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣
መ/ ከግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ስለግብር አከፋፈል የሚገልጽ በጨረታ ላይ ለመሳተፍ የሚያስችል የታክስ ክሊራንስ ማረጋገጫ፣
ሠ/ በመንግስት የዕቃና የአገልግሎት ግዢዎች ላይ ለመሳተፍ በመንግስት ግዢ ኤጀንሲ ድህረ ገጽ ላይ የተመዘገቡበትን ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው፡፡
ረ/ በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ድርጅቶች ለ2013/2014 ዓ.ም በጀት ዓመት የታደሰ የማይክሮ ኢንተርፕራይዝ ምስክር ወረቀት ማቅረብ አለባቸው

1ኛ.ተጫራቾች የጨረታውን ሰነድ ከታች በተገለጸው አድራሻ በዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ ክፍል ለእያንዳንዱ ሎት የማይመለስ ብር 100/አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ዘወትር በሥራ ሰዓት ሕንጻ ቁጥር 106 ግዢና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 04 በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡

2ኛ.ተጫራቾች ከላይ ለተገለፁት እቃዎች ለተ.ቁ 1፣2 አንድ የቴክኒክ ሰነድ ኦርጂናል፤ አንድ ቴክኒክ ሰነድ ኮፒ አንድ የፋይናንስ ኦርጂናል እና አንድ የፋይናንስ ሰነድ ኮፒ ለየብቻ በማሸግ ከተ.ቁ 3-12 አንድ የፋይናንስ ኦርጂናል እና አንድ የፋይናንስ ሰነድ ኮፒ ለየብቻ በማሸግ ለተጠቀሰው የግዢ ዓይነት ከጨረታ ሰነዶቻችሁ ጋር አባሪ አድርገው የተጠየቁትን ማስረጃዎች በማሟላት የድርጅቱን ማህተምና ፊርማ በሁሉም ገጾች ላይ በማኖር ለፋይናንስ እና ለቴክኒክ መወዳደሪያ ኦሪጂናልና ኮፒ ለየብቻ በማድረግ የታሸጉ ፖስታዎችን መመለስ ይኖርባቸዋል።

3ኛ.በተ.ቁ 1፣2 ለተጠቀሱት ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ቢድ ቦንድ 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር)፣ በተ.ቁ 3-8 ለተጠቀሱት 30,000 (ሰላሳ ሺህ ብር) ፣ በተ.ቁ 9-10 ለተጠቀሱት 20,000 (ሃያ ሺህ ብር) እና በተ.ቁ 11-12 ለተጠቀሱት 10,000 (አስር ሺህ ብር) በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ፣ለ90 ቀናት የሚቆይ የባንክ ዋስትና (ጋራንቲ) በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ስም አዘጋጅተው ወይንም በጥሬ ገንዘብ ለዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ በመክፈል ከጨረታ ሰነዱ ጋር አባሪ አድርገው በተሰጠው ስፔስፊኬሽን ላይ በመሙላትና የድርጅቱን ማህተምና ፊርማ በሁሉም ገጾች ላይ በማኖር ኦሪጂናል እና ኮፒ ፖስታዎችን በሰም በታሸገ በተለያዩ ፖስታ በማድረግ መመለስ ይኖርባቸዋል፡፡

4ኛ.ጨረታው ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በ16ኛው ተከታታይ ካላንደር ቀን የሚከፈት ይሆናል (በጨረታ ሰነድ የመጀመሪያው ገጽ ላይ ይመልከቱ)። ተጫራቾች የመወዳደሪያ የጨረታ ሰነዱን ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስታወቂያው ይፋ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ ጨረታው እስከሚታሸግበት ሰዓት ድረስ የጨረታ ሰነዱን ለዚሁ አገልግሎት በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ መመለስ ወይንም ማስገባት ይችላሉ። ጨረታው የሚከፈትበት 16ኛው ካላንደር ቀን ቅዳሜና እሁድ ወይም የሕዝብ ባአላት ቀን ላይ ከዋለ ጨረታው የሚከፈተው በሚቀጥለው የሥራ ቀን በተጠቀሰው ሰዓት ነው።

5ኛ.ዝርዝር መረጃውን በተመለከተ ተጫራቾች የተዘጋጀውን የጨረታ ሰነድ ገዝተው ማየት ይችላሉ። ዩኒቨርሲቲው የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለተጨማሪ ማብራሪያ የዩኒቨርሲቲው ድህረ ገጽ www.astu.edu.et በመጎብኘት የጨረታውን ዝርዝር መመልከት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በስልክ ቁጥር 0222110003/0222110094 ደውሎ በመጠየቅ አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

## የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ

# የቱሪዝም ዘርፉ ተስፋዎች- ሁሉን አቀፍ እድገት የማስመዝገብ ግብ

**ዳግም ከበደ**

ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛ ነች። ከ3 ሚሊዮን ዓመታት በላይ እድሜ ያስቆጠረው "የሉሲ" ወይም ድንቅነሽ አፅም መገኛ። የአረቢካ ቡና ዝርያ፣ የዓለማችን ረጅሙ ወንዝ ጥቁር አባይም፣ የኤርታአሌ የእሳተ ገሞራ ሀይቅና የዓለማችን እጅግ ረባዳና ሞቃት ስፍራ ዳሎል በኢትዮጵያ ይገኛሉ። ምን ይሄ ብቻ! ኢትዮጵያ የንግስት ሳባ አገር ነች፣ በርካታ የስምጥ ሸለቆ ሃይቆችና ፍል ውኃዎች፣ እንዲሁም የዱር እንስሳት ፓርኮችና ጥብቅ ቦታዎች ይገኛሉ። ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊ፣ ሰው ሰራሽና ባህላዊ ቅርሶችን በዩኔስኮ በማስመዝገብ በአፍሪካ ቀዳሚዋ አገር ለመሆን በቅታለች። ኢትዮጵያ በተፈጥሯዊ፣ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶች የበለፀገች፣ የቱሪስት መስህብ ያላት ብትሆንም ቱሪዝሙ በተለይ ዜጎች የራሳቸውን አገር እና ሃብት የመጎብኘትና የማወቅ ባህል በሚፈለገው ልክ አለመሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ።

የቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያ ዶክተር ተስፋዬ ዘለቀም ይህንኑ ነው የሚያረጋግጡት። እርሳቸው እንደሚሉት ኢትዮጵያ እምቅ የቱሪዝም ሃብት ካላቸው አገራት በቀዳሚነት የምትመደብ ነች። በተለይ ከአፍሪካ ቀዳሚ ሃብት ያላት አገር ነች። ከምድር በላይ ከሰማይ በታች ያለው ማንኛውም ነገር የቱሪዝም እምቅ ሃብት ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ታሪካዊ እንዲሁም ተፈጥሯዊ የሆኑ ሃብቶች እንዳሉ ይታወቃል። ከእኛ የሚጠበቀው ትልቁ ሥራ እነዚህን እምቅ ሃብቶች ወደ ቱሪዝም ምርትና አገልግሎት ቀይሮ ለዓለም አቀፍና የአገር ውስጥ ቱሪስቶች ማበርከት ነው። መንግሥትም ሆነ በቱሪዝም ዙሪያ የሚሰሩ የግል ዘርፉ አንቀሳቃሾች ይህን ኃላፊነት ሊወጡ ይገባል። የትምህርት ተቋማትም ይህንን ያገናዘበ ስርዓተ ትምህርት ቀርፀው ብቁ የሰው ሃብት ማፍራት ይኖርባቸዋል። ከምንም ነገር በላይ ኢትዮጵያ ለዓለም ያበረከተቻቸው እንደ መስቀል፣ ጥምቀት፣ ኢሬቻ፣ እና ሌሎችም የተፈጥሮና የሚዳሰሱና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባለቤት ነን። በመንግስት እየተሰሩ ሜጋ የቱሪዝም ፕሮጀክቶችም ተጨማሪ የቱሪዝም ሃብቶች መሆናቸውን ገልፀው ፀጋውን ወደ ግዙፍ ኢኮኖሚያዊ አቅም ለመቀየር መስሥራት እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ።

ይህንን የተረዳው መንግሥትም በተጠናና በፖሊሲ በተደገፈ መልኩ ከዓመት በፊት ቱሪዝምን ከቁልፍ የኢኮኖሚ ዘርፎች ውስጥ አንዱ አድርጎ ማካተቱን ይፋ አድርጓል። ከዚህ በተጨማሪ አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻ ሜጋ ፕሮጀክቶችን እና መሰረተ ልማቶችን እየገነባ ይገኛል። በዋናነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የበላይ ጠባቂነትና ጥንስስ ሀሳብ በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ስፍራዎች ግዙፍ የቱሪዝም ፕሮጀክቶች እየተገነቡ ይገኛሉ። በተጨማሪ የቱሪዝም ምርትን በማሳደግ፣ ገበያና የማስተዋወቅ ስራውም በእውቀትና በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ለማድረግ ስትራቴጂ ተነድፎ በሥራ ላይ እንዲውል መደረጉን መንግሥት ይፋ አድርጓል።

ከቀናት በፊት ለህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ማብራሪያ ለመስጠት ብቅ ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከቅርብ ግዜ ወዲህ ዘርፉን ለማሳደግና አገሪቱን የኢኮኖሚ ተጠቃሚነቷን ከፍ ለማድረግ እየተሰሩ ያሉትን ሥራዎች አንስተው ነበር። በተጨማሪ ዘርፉ እየገጠመው ያለውን ፈተናና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችንም እንደሚከተለው አስቀምጠዋል።

### ቱሪዝም አእማድ ዘርፍ

በምክር ቤቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የቱሪዝም ዘርፍ የብልፅግና አእማድ ከሆኑ ዘርፎች ውስጥ አንዱ መሆኑን አንስተዋል።ይህ የሆነበት ምክንያት ሲያስረዱም በማለት ገለፃ አድርገዋል። የአገልግሎት ዘርፉ በጣም እያደገና እየሰፋ የሚሄድ መሆኑን አረጋግጠው፤ ኢትዮጵያ የቱሪዝም እምቅ አቅም በጣም በስፋት ያላት እንደሆነች ተናግረዋል። በዚህ ላይ በትኩረት መሥራት ከተቻለ ያለጥርጥር ውጤት ማምጣት እንደሚቻል ነው ከገለፃቸው መረዳት የሚቻለው።

> ጎርጎራ ብቻ ግን ብቻውን አለመሆኑን በመግለፅም ከጎርጎራ ሰላሳ ደቂቃ ባህር ላይ መሄድ ቢቻል ዳጋ ላይ በብዙ አለማት ልናያቸው የማንችላቸውን ታሪኮች ማግኘት እንደምንችል እነዚህም የቱሪዝም እሴቶች መሆናቸውን መስክረዋል፡፡የአፄ ፋሲልና የአፄ ሲሲኒዮስ አስክሬን መቃብር እስካሁን ድረስ ልክ እንደ ሰው ከእነ ስማቸው ከነዘመናቸው መቀመጡንም ነው የተናገሩት

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ውስጥ እጅግ በርካታ ሃብቶች መኖራቸውንም አንስተው ይህንን መገንዘብ እንደሚያስፈልግ በመግለፅ ሃብቱን ዜጎችን እና አገርን ሊጠቅም በሚችል መልኩ መለወጥ እንደሚገባ ገለፃ አድርገዋል። እንደ እርሳቸው ማብራሪያ ኢትዮጵያ አንደኛ ባህል፣ ሁለተኛ ታሪክ፣ ሶስተኛ ታይተው የማይጠገቡ ቦታዎች አሏት።

### አሁን ምን እየተሰራ ነው?

ጠቅላይ ሚኒስትሩ መንግሥት ከቅርብ ግዜ ወዲህ ለቱሪዝም ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት በርካታ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑን ገልፀዋል። ከግዙፍ የግንባታ ፕሮጀክቶችና የመዳረሻ ልማቶች በተጨማሪ ቅርሶችን መጠገንና መንከባከብ ላይም ትኩረት መደረጉን ተናግረዋል። በምሳሌነትም የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናትን አንስተዋል።

"ላልይበላ እጅግ አስደማሚ የሆነ ሥራ ነው።መጠነኛ ችግር ገጥሞታል" ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ። ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር ሆነን ለመጠገን ብዙ ሥራ እየተሰራ እንደሚገኝ ያስረዳሉ።የነበረው ቅርስ ሳይፈርስ መቆየት እንዳለበትም ይናገራሉ።በተመሳሳይ አክሱም ከጣሊያን መንግሥት ጋር በትብብር ለመጠገን ጥናት ከተጀመረ በኋላ የሰላም ችግር መፈጠሩንና መጓተት እንዳጋጠመው ነው የሚገልፁት። ሰላም ሲመጣ የጥገና ሥራው የሚቀጥል መሆኑንም ተናግረዋል።ሌላው ደግሞ ብሄራዊ ቤተመንግሥት በከፊል ከፈረንሳይ መንግሥት ጋር (ፕሬዚዳንት ማክሮን አግዘው) በከፊል ደግሞ አንድነት ፓርክ ከተከፈተ ጀምሮ በርከት ያለ ሃብት እያስገባ በመሆኑ በዚያ 300 ሚሊዮን ብር ተመድቦ በታችኛው ቤተመንግሥት ላይ ኢንቨስት እየተደረገ ነው።ራሱ ገቢውን ችሎ ፅዳቱን ጠብቆ 300 ሚሊዮን ብር ደግሞ ታችኛው ቤተመንግሥት ኢንቨስት አድርጎ በጣም ዘመናዊ የመኪና ኤግዚቢሽን እየሠራ ነው።ይህ ተጨማሪ የቱሪዝም መዳረሻና የገቢ ምንጭ የሚሆን ነው ብለዋል።

### አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎች

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ በመንግሥት ቁርጠኝነት አዳዲስ የቱሪዝም መዳረሻዎች እየተፈጠሩ መሆኑን ተናግረዋል። በቅርቡም "ዩኒቲ የመኪና ኤግዚቢሽን" እንደሚሠራ ይፋ አድርገዋል።የፈረንሳይ መንግሥት ባደረገው ትብብርና እገዛ መነሻም ቤተመንግሥቱ በጣም በፍጥነት እየታደሰ መሆኑን ገልፀዋል።ሥራው ተገባዶም በሚቀጥለው ዓመት መስከረም ለህዝብ ክፍት እንደሚሆን ነው ቃል የገቡት፡፡

"ታችኛው ቤተመንግሥት በከፊል ወርቁም፣ መፅሃፉም፣ ታሪኩም፣ መኪናውም ለቱሪስት መስህብ ሆኖ በምናስበው ደረጃ ከወጣ እጅግ አስደማሚ ቦታ ነው" የሚሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ ይህን የሚያክል ነገር አላት ወይ? ብለው ሰዎች እንዲጠይቁ የሚያደርግ መሆኑን አስረድተዋል።ነገር ግን ቱሪዝም የነበረውን በማዘመንና በመጠገን ብቻ የሚሆን ነገር የለም በማለትም አዳዲስ ግንባታ እና የመዳረሻ ስፍራዎችን ማልማት እንደሚገባ ተናግረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመንግሥት ተነሳሽነት ከሚሰሩ አዳዲስ የቱሪዝም ሥራዎች መካከል ጎርጎራን በምሳሌነት አንስተው እጅግ ግዙፍ እጅግ በጣም ውብ ሥራ መሆኑን መስክረዋል። ጎርጎራ ብቻ ግን ብቻውን አለመሆኑን በመግለፅም ከጎርጎራ ሰላሳ ደቂቃ ባህር ላይ መሄድ ቢቻል ዳጋ ላይ በብዙ አለማት ልናያቸው የማንችላቸውን ታሪኮች ማግኘት እንደምንችል እነዚህም የቱሪዝም እሴቶች መሆናቸውን መስክረዋል።የአፄ ፋሲልና የአፄ ሲሲኒዮስ አስክሬን መቃብር እስካሁን ድረስ ልክ እንደ ሰው ከእነ ስማቸው ከነዘመናቸው መቀመጡንም ነው የተናገሩት።ይህን በየትኛውም ዓለም ላይ የሚገኝ ኪንግደም ሊያሳየን አይችልም ይላሉ።

"የትም ብትዞሩ እንዲህ አይነት እውቀት በቀላሉ ሊገኝ አይችልም" የሚሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ እዳጋ እስጢፋኖስ ሲኬድ በጣም በርካታ ታሪኮችን ቱሪስቱ ማግኘት እንደሚችል ያስረዳሉ።ሰው ጎርጎራ ሲሄድ ታሪክ ይማራል፤ እጅግ የሚያምር ሃይቅ ያያል፣ በውሃ ላይም የሚያዝናኑ ድርጊቶች ላይ ይሳተፋል፣ ባማረ ቦታ ማረፍ ይችላል በማለትም ከዚያም ራቅ ብሎ ባህርዳር፣ ጎንደር የመሄድና የመጎብኘት እድል አለው ይላሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህንን ሁሉ ሃብት ወደ ቱሪዝም መዳረሻነት መቀየር እንደሚያስፈልግ መንግሥት ተረድቶ በርካታ ሥራዎችን እየሠራና ፕሮጀክቶቹን ይፋ እያደረገ መሆኑን ተናግረዋል። ይህንን ሁሉ ማያያዝ ሲቻል ቱሪስት ተስቦ ወደ ቦታው እንደሚሄድ እንዲሁም በቀላሉ በርካታ ጎብኚዎችን መሳብ እንደሚቻል አንስተው ይህ እውን የሚሆነው ግን "ዳጋ ላይ እንዲህ አይነት ታሪክ አለ" ስላልነው ሳይሆን ማረፊያ ማዘጋጀትና መዳረሻዎችን ምቹ አድርጎ በማልማት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

"ትራንስፖርት ከሌለ ወደ መዳረሻዎች ጎብኚዎች አይሄዱም።ግንባታ ያስፈልጋል።ለእርሱም እየገነባን ነው" የሚሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ብዙዎቹ ፕሮጀክቶች እያለቁ እንደሚገኙ ተናግረዋል። ጊዜው ሲደርስ እየተመረቁ ለጎብኚዎች ክፍት እንደሚሆኑም ነው የተናገሩት።ከግንባታ እና ጥገና ውጭ ግን የቱሪዝም አገልግሎት ዘርፉ መሻሻል እንደሚያስፈልገው ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የሚገኙትን የቱሪዝም መዳረሻዎች በተገቢው ማወቅ፣ ማልማት እንዲሁም ማስተዋወቅ ሲቻል ሁሉን አቀፍ የቱሪዝም እድገት ማምጣት እንደሚቻል ነው ለህዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት ማብራሪያቸውን የሰጡት።

### እንደ መውጫ

ከላይ ለማንሳት እንደሞከርነው ኢትዮጵያን ከዓለም ቀዳሚ ከሆኑ የቱሪዝም መዳረሻ አገሮች መካከል እንድትመደብ መንግሥት እየሠራ መሆኑን ይገልፃል። ለተፈፃሚነቱም የተለያዩ ህጎችን በማርቀቅና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ ይፋ እያደረገ ይገኛል። ሜጋ የቱሪዝም ፕሮጀክቶችን የመገንባት ሂደቶችም እየታዩ ነው። ስር ነቀል የአደረጃጀት ለውጥ ማድረግም አንዱ ነው። እምቅ የቱሪዝም ሃብቶችን በገበያ ልማትና ፕሮሞሽን በማገዝ የጎብኚዎች መዳረሻ እንዲሆኑ ከማድረግ በተጨማሪ አዳዲስ የመስህብ ስፍራዎችን ማስተዋወቅ ዋንኛ ሥራው መሆኑም ይታወቃል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በዘርፉ ሌላኛው የመንግሥት ዋንኛ ግብ አካታች ቱሪዝምን መገንባት ነው። ቱሪዝም ለጎብኚዎች የመስህብ ስፍራዎችን ማስቃኘት ብቻ ሳይሆን አገር ከዚያ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል ነው። በጥቅሉ የአገር ኢኮኖሚ ያድጋል እንበል እንጂ እያንዳንዱ ዜጋ የድምር ውጤቱ ተቋዳሽ መሆኑ የማይቀር ነው። በቅንጅትና ሁሉንም ባሳተፈ መልኩ የሚገነባው የቱሪዝም ዘርፍ ደግሞ በጥቅሉ ኢትዮጵያን በውብ መዳረሻነትና የላቀ ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ላይ የሚያደርስ ነው። ይህ ሲሆን ሁሉን አቀፍ (አካታች) የቱሪዝም እድገት ተገንብቷል ማለት እንችላለን። ይህንን መነሻ በማድረግም መንግሥት፣ ዜጎችና ዘርፉ የሚመለከታቸው ሁሉም አካላት ለተፈፃሚነቱ በጋራ ሊሰሩ ይገባል እንላለን። ሰላም!

# ስፖርት





# የትንሿ አገር ትልቅ ዓለም አቀፍ ድግስ

**ብርሃን ፈይሳ**

የዓለም ህዝብ የመግባቢያ ቋንቋ የሆነው የእግር ኳስ ትልቁ ውድድር ዓለም ዋንጫ፤ ዛሬ በአረብ ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ ይካሄዳል። ትንሿ አገር ኳታር እጅግ ከፍተኛ መዋለነዋይ ያወጣችበትን 22ኛውን የዓለም ዋንጫ በደማቅ ሁኔታ ታስጀምራለች። ባህላዊውን የአረብ ጎጆ ቅርጽ የያዘውና በሰሜን ዶሃ የተገነባው ግዙፉ የአል ባይት ስታዲየም ደግሞ የዛሬውን የመክፈቻ መርሃ ግብር ያስተናግዳል።

በዚህ ተናፋቂ በሆነው የዓለም ዋንጫ አዘጋጇ ኳታር ለመጀመሪያ ጊዜ የውድድሩ ተካፋይ ትሆናለች። ብራዚላውያን ደግሞ ስድስተኛውን ዋንጫ በማንሳት ክብረወሰኑን ከእጃቸው ላለማውጣት ይፋለማሉ። በቅርቡ ንግስታቸውን ያጡት እንግሊዛውያንም እአአ ከ1966 ወዲህ ያላነሱትን ዋንጫ ኳታር ላይ ለማንሳት ተስፋ አድርገዋል። የወቅቱ የዓለም የእግር ኳስ ኮከብና ጠበብቶች ሊዮኔል ሜሲና ክርስቲያኖ ሮናልዶ ምናልባትም ከዚህ በኋላ በማይሳተፉበት በዚህ ውድድር በዋንጫ የታጀበ ታሪክ ለማስመዝገብ ወጥነዋል። ወጣት ተጫዋቾችም ብቃታቸውን ለማሳየት ለአገራቸውም ዋንጫውን ለማንሳት ጅማሬውን ዛሬ በሚያደርገው የዓለም ዋንጫ ተሰይመዋል።

ከዛሬ ጀምሮም ከ32 ብሄራዊ ቡድኖች የተወጣጡ ከ800 በላይ የእግር ኳስ ተጫዋቾች በስምንቱ የኳታር ስታዲየሞች የዋንጫ ፉክክራቸውን ያካሂዳሉ።




እአአ የ2019 የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮናን ያስተናገደችው ትንሿ አገር ኳታር ይህንን ውድድር ተከትሎ ለስታዲየሞች፣ ለሆቴሎች፣ ለመንገድና ሌሎች መሰረተ ግንባታዎች ከ220 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር አውጥታለች። ይህ ደግሞ እስካሁን ከተካሄዱ የዓለም ዋንጫዎች መካከል ውዱ አድርጎታል።

እምብዛም የእግር ኳስ ታሪክ የሌላት ኳታር ሰባት ስታዲየሞችን ለዚህ ውድድር ያስገነባች ሲሆኑ፤ በጀርመናዊው አርክቴክት አልበርት ስፒር እና ባልደረቦቹ የተነደፉም ናቸው። ግዙፍና እጅግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው ስታዲየሞቹ እያንዳንዳቸው ከ40ሺ እስከ 80ሺ ደጋፊዎችን የሚያስተናግዱም ናቸው። አስገራሚው ነገር ደግሞ አገሪቷ እጅግ ትንሽ ከመሆኗ የተነሳ በእያንዳንዱ ስታዲየም መካከል ያለው ልዩነት ከ60 ኪሎ ሜትር አይሰፋም፤ ሩቅ የሚባለው ብቸኛው ስታዲየም ርቀትም ቢሆን 90 ኪሎ ሜትር በመሆኑ ደጋፊዎች በቀላሉ የሚፈልጉትን ጨዋታ በቅርብ ርቀት ተመልክተው ወደ ሌሎች ስታዲየሞችም የመጓዝ እድልን የሚያስገኝላቸው ይሆናል።

ኳታር እጅግ ከፍተኛ የሚባል ሙቀት ያለባት አገር እንደመሆኗ ቀን ቀን ሙቀቱ በተለየ ሁኔታ ያይላል። ታዲያ ይህ ሁኔታ ውድድሩን በበላይነት ለሚመራው ፊፋም ሆነ ለእግር ኳስ ቤተሰቡ አሳሳቢ እንደመሆኑ ኳታር በተለየ ትኩረት የሰራችበት መሆኑን ነው ያሳወቀችው። ይኸውም በስምንቱም ስታዲየሞች የአየር ማቀዝቀዣ ቴክኖሎጂዎችን ዝግጁ በመደረጋቸው በሜዳ ላይ ለተጫዋቾችም ሆነ ለተመልካች ስጋቱ የሚቀረፍበት መንገድ ተመቻችቷል።

በዚህ የዓለም ዋንጫ በፊፋ በኩል 36ዳኞች፣ 69 ረዳት ዳኞች፣ 24 የቪድዮ ዳኞች ዝግጁ መሆናቸው ታውቋል። ካለፈው ጊዜ ለየት የሚያደርገው ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ሴት ዳኞች የተካተቱበት የወንዶች ዓለም ዋንጫ በመሆኑ ነው። እንስቶቹ ዳኞች ሶስት ሲሆኑ፤ ፈረንሳዊቷ ስቴፋኒ ፍራፖርት፣ ሩዋንዳዊቷ ሳሊማ ሙካንሳንጋ እና ጃፓናዊቷ ዮሺሚ ያማሺታ ናቸው። የዓለም ዋንጫ አስቀድሞ በሚካሄድበት የፈረንጆቹ በጋማ ወቅት በረሃማዋ ኳታር እጅግ አስቸጋሪ የአየር ሁኔታ የምታስተናግድበት እንደመሆኑ ፊፋ ወደ ህዳር ወር ሊቀይረው ችሏል። አጭሩ የዓለም ዋንጫ የተሰኘው የኳታሩ የዓለም ዋንጫ 64 ጨዋታዎችን በ28 ቀናት አካሂዶ ለማጠናቀቅ ነው የታቀደው። ኳሷ በአዲዳስ የተመረተች ሲሆን፤ መጠሪያውም «አል ሪህላ» ጉዞው የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑም ታውቋል።




# የሒሳብ ትምህርት ተሸላሚዋ ሶሊያና

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ትምህርት እንዴት ይዟችኋል? በደንብ እያነበባችሁ ነው አይደል? ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል። ማንበብ የተሻለ አቅም ለመፍጠርም ሁነኛ መፍትሄ ነው። ማንበብ ፍላጎታችሁን ለማሳካትም ወሳኝ ነው። ስለዚህም ሁልጊዜ አንባቢ መሆን አለባችሁ። ጨዋታችሁ ጭምር ከንባብ ጋር መገናኘት አለበት። ምክንያቱም ማንበብ መፅሐፍትን ብቻ ሳይሆን የምንሰራውን ሥራ ጭምር ነው። እናም ውጤታማና ጎበዝ ተማሪ መሆን ከፈለጋችሁ ጥሩ አንባቢ መሆን ይኖርባችኋል። በማንበባችሁ ተጨማሪ እውቀትን ማዳበር ትችላላችሁ።

ልጆች ማንበብ ከስልጠና ጋር ሲሆን ደግሞ የተሻለ አቅም ለመገንባት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ስልጠና እየወሰደች ራሷን ያበቃችውና በጣም ጎበዝ ተማሪ የሆነችውን ልጅ ለዛሬ እንግዳ አድርጌ አቅርቤላችኋለሁ። ተማሪ ሶሊያና አባይነህ ትባላለች። በኪዳነምህረት ትምህርት ቤት የአራተኛ ክፍል ተማሪ ናት። በትምህርቷ ደግሞ በጣም ጎበዝ በመሆኗ መምህራኖቿ፣ ወላጆቿ፣ ጓደኞቿ ሁሉ ይወዷታል።

ሶሊያና ጎበዝ የሆነችበት ምክንያት በሁለት መልኩ እንደሆነ ታምናለች። የመጀመሪያው ትምህርቷን በአግባቡ መከታተሏና የተለያዩ ስልጠናዎች ላይ መሳተፏ ናቸው። ለአብነት ሽልማት ያገኘችበት «የአቫከስ» ስልጠና አንዱ ነው። አቫከስ የሚባለው ስልጠና ተማሪዎች በሒሳብ ትምህርታቸው የላቁ እንዲሆኑ የሚያደርግ ስልጠና ሲሆን፤ በየክልሉ ይከናወናል። እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚደረገው ውድድር ላይ እርሷ ተሳታፊ ነበረችና ሁለተኛ በመውጣት ዋንጫ ተሸልማለች። በዚህ ስልጠና የሚሳተፉት ተማሪዎች በጣም በርካታ ናቸው። ከብዙ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ ናቸው። ስለዚህም እነርሱን ሁሉ አሸንፋ ነው ለሽልማት የበቃችው።

ሶሊያና ስልጠናውን በመውሰዷ ብዙ ተጠቅማለች። አንዱ ፈጣንና ቀልጣፋ ተማሪ እንድትሆን አስችሏታል።



**ተማሪ ሶሊያና አባይነህ**

ሌላው ደግሞ ማባዛት፣ መደመር፣ መቀነስና ማካፈልን በቃሏ ጭምር እንድትተገብረው አድርጓታል። በጣም ከባድ ናቸው የሚባሉ ቁጥሮችን ሳይቀር በስሌቶቹ መሰረት ትሰራቸዋለች። በተለይ ደግሞ የማስተዋልና የማስታወስ ችሎታዋ ከጊዜ ወደጊዜ እንደጨመረላት ትናገራለች። ለዚህ ማረጋገጫው ደግሞ መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ ቀድማቸው መልሱን መመለሷ ነው።

ልጆች ሶሊያና ታናሽ ወንድሟንም ታስጠናዋለች። በዚህም የተሻለ አቅሟን ገንብታለች። እንደውም በጋራ መስራትና ማንበብ ለበለጠ ውጤታማነት አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አላት። ይህንን እምነቷን ደግሞ ትምህርት ቤት ጭምር ትጠቀምበታለች።

ሶሊያና ትምህርቷን በምታጠናበት ጊዜ የተለየ ዘዴ ትጠቀማለች። ይህም የተለየ የሥዕል ችሎታ አላትና እርሱን በመጠቀም የማትረሳበትን መንገድ ትፈጥራለች። ሁልጊዜም ስዕሎችን ስትሰራ አብስትራክት አድርጋ ነው። ይህ ደግሞ ለመመራመር አመቺ ነውና ያስደስታታል።

ልጆች ሶልያና ምን መሆን እንደምትፈልግ ታውቃላችሁ? ምኞቷ ኢንጅነር መሆን ነው። ምክንያቷ ደግሞ በጣም ያስገርማል። ምን መሰላችሁ በመንገድ ላይ ስትሄድ ብዙ ጊዜ ጎዳና ላይ ተኝተው ሰዎችን ታያለች። የሚለብሱት ልብስም በጣም ያሳዝናታል። ብርዱን እንዴት ይቋቋሙታል የሚለውም የሁልጊዜ ጭንቀቷ ነው። እናም ይህንን መፍትሄ መስጠት ትፈልጋለችና ኢንጂነር መሆንን ተመኘችው። ምክንያቱም የዚህ ሙያ ባለቤት ስትሆን ቤት መገንባት ትችላለች። ስለዚህም ለእነዚህ ድሆች ቤት በመስራት እፎይታ ለመስጠት ታስባለች። ህልሟን ለማሳካት ደግሞ ከአሁኑ ጀምራ የሳይንስ ዘርፉ ላይ ትኩረቷን አድርጋ ትሰራለች።

እንደ ሶሊያና እምነት ልጆች የተለየ ስጦታ አላቸው። ስጦታቸው ግን የሚዳብረው በአንድ ነገር ነው። ስኬታማ ለመሆን ጠንክረው ሲሰሩና የተባሉትን ሲያደርጉ ነው። በተለይም ወላጆቻቸውን ማክበርና ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል የሁልጊዜ ሥራቸው መሆን አለበት። የሚሰጧቸውን እድሎችም መጠቀም ይጠበቅባቸዋል። ለአብነት ቤተሰብ የተሻለ አቅም እንዲፈጥሩ ብሎ ብሩን ከፍሎ ሲያስተምራቸው እነርሱ የተሻሉ ሆነው መገኘት አለባቸው።

ሶልያና ለእናንተ ለልጆች የምትመክረው ነገር አላት። ይህም ፍላጎታችሁን ሊያሳካላችሁ የሚችል የትምህርት መስክ ሊኖራችሁ ይገባል የሚል ነው። ለእርሷ ሒሳብ ትምህርት የተሻለ ስኬትን እንደሚሰጣት ታምናለች። ምክንያቱም ብዙ ነገሮች መፍትሄ የሚያገኙት በሒሳብ ቀመር ነው ብላ ታስባለች። በዚያ ላይ በሁሉም ትምህርት ውጤታማ የመሆኗ ምስጢር በዚያ ላይ ትኩረቷን አድርጋ መስራቷ እንደሆነ ታምናለች። እናም ልጆችም ለቆሙለት አላማ መታገልና መትጋት አለባቸው የሚል ምክር አላት።

ሌላው ያነሳችው ነገር ብቻቸውን ምንም ነገር ማድረግ የለባቸውም የሚለውን ነው። በጋራ በመስራታቸው የማያውቁትን ያውቃሉ፣ አዲስ ነገር ለመፍጠር ይነሳሳሉ፣ ክፍተቶቻቸውን ይደፍናሉ። ስለዚህም አብሮ መስራትንና ማጥናትን ቢለማመዱት ትላለች። በተጨማሪም ተጨማሪ ትምህርት በሚማሩበት ጊዜ ሳይጨናነቁ መሆን አለበት። ምክንያቱም በመጨናነቅ ውስጥ መርሳት ይኖራል። ስለሆነም ራሳችሁን የምታሳርፉበትን ዘዴ መፍጠር ይኖርባችኋል ስትል ትመክራለች። ለምሳሌ እርሷ እስከ 11፤30 ትምህርት ቤት ውስት ትቆያለች። ከትምህርት ቤት በኋላ ግን ዘና የሚያደርጓትን ተግባራት ነው የምትፈጽመው። ስለዚህም ጨዋታ፣ ንባብና የቤት ሥራ መስራት እንደየድካማቸው መጠን መጓዝ እንዳለባቸው ታሳስባለች።

ልዩ ችሎታን አውቆ መስራት የፈጠራ ሥራ ለመስራት ወሳኝ ነገር ነው። ስለዚህም መነሻችሁ መሆን ያለበት ምን መስራት እችላለሁ የሚለውን መረዳት ነው። ከዚያ ለእርሱ የሚሆነውን ሙከራ በየጊዜው ማድረግ ይኖርባችኋል። በተለይም ከትምህርታችሁ ጋር አያይዛችሁ ለመስራት ከሞከራችሁ ውጤታማ ትሆናላችሁም ባይ ናት።

ተሸላሚ መሆን በቤተሰብ ብቻ ሳይሆን በመምህራንና በሌሎች አካላት ተወዳጅ ያደርጋችኋል። ጎበዝ ተማሪ የምትሆኑበትን መንገድም ይጠርግላችኋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ችግር ፈቺና ለአገር ጠቃሚ ሰው እንድትሆኑ በር ይከፍትላችኋል። ችግር ፈቺነታችሁ ደግሞ ከአካባቢያችሁ የሚጀምር ነውና የፈጠራ ሥራ ስትሰሩ ይህንን እያሰባችሁ አድርጉ ምክሯ ነው። ምክሯን እንደምትተገብሩት በማመን ለዛሬ የያዝነው እንቋጭ። በሚቀጥለው ሳምንት በሌላ ሀሳብና እንግዳ እስክንገናኝ ቸር ሰንብቱ።